# የአካባቢ ሳይንስ

## የመምህራን መምሪያ

## ሁለተኛ ክፍል


### አዘጋጆች

ጋዲሳ በዳዳ ቲጃኒ ሁሴን

ንጉሴ ለማ ዘውዱ ቱሉ

### አርታኢዎች

አሰግድ ደረጄ ጉታ ሁንዴ

ፍቃዱ ከበደ ታርኩ ዲጋ

ግርማዬ ደፋር

### ገምጋሚዎች

አሸብር መኮንን ብርሃኑ ለታ

ዘውዴ ረጋሣ

### ተርጓሚዎች

አበራ ከበበው

ታደሰ ዱሬሳ

### ግራፍክስ

ታደሰ ድንቁ

### እሉስቱሬተር

ቡዛዮ ግርማ

## ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምዕራፍ 1: ሳይንስን ግልጽ ማድረግ........................................ 1
1.1 የሰውነታችን ውጫዊ አካል ክፍሎችና የስሜት አባለ አካላቶቻችን........................................ 1
1.2 ልዩ ቁሶችን መለየት........................................ 4
1.3 የብርሃን ምንጮች........................................ 7
ምዕራፍ 2 ፡ መገኛ........................................ 10
2.1 የመገኛ ምንነት........................................ 11
2.2 የአንፃራዊ መገኛ ምንነት........................................ 13
2.3 የወረዳችን አንፃራዊ መገኛ........................................ 14
2.4 በወረዳችን የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎች........................................ 15
2.5 የወረዳችን ቀበሌዎች መገኛና ስማቸው........................................ 16
ምዕራፍ 3: የተፈጥሮ አከባቢ........................................ 18
3.1. የአየር ጠባይ እና የአየር ንብረት........................................ 19
3.2. የወረዳችን ዕፅዋት........................................ 23
3.3. የወረዳችን እንስሳት........................................ 26
3.4. የወረዳችን የተፈጥሮ ሀብቶች........................................ 29
3.5. የወረዳችን የአከባብ ጥበቃ........................................ 31
ምዕራፍ 4: ማህበራዊ አከባቢ........................................ 36
4.1 የቤተሰብ አባላትና ለቤተሰብ የሚያስፈልጉ ተግባራት........................................ 36
4.2 የትምህርት ቤት ማህበረሰብ በጋራ ሊያከናውኑ የሚችሉት ተግባራት........................................ 38
4.3 የግልና እና የትምህርት ቤት ንፅህናን መጠበቅ........................................ 40
ምዕራፍ 5: ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች........................................ 43
5.1. በመኪና መንገድ ላይ የሚደረግ ጥንቃቄ........................................ 43
5.2. የራስን ጤንነት መጠበቅ........................................ 45
**መርሃ ትምህርት ........................................47**

## አጠቃላይ መግቢያ

የተፈለገው ግብ ላይ ለመድረስ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን መማር ማረጋገጥ በጣም ወሳኝ ነው። በአሁኑ ጊዜ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ተማሪን ያማከለ ቢሆንም መምህሩ/ርቷ የእያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎ በመከታተል ማገዝ፣ መምራት፣ መንገድ ማሳየት እና ማበረታታት ይኖርበታል/ባታል። ስለዚህ በትምህርት ሂደት ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች ሐሳብ መስጠት፣ መወያየት እና በጋራ በመስራት ዕውቀት፣ ግንዛቤ እና ያላቸውን ክህሎት በመለዋወጥ የሚፈለገው የትምህርት ውጤት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ ያስፈልጋል።

መምህራን አሳታፊ የሆነ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መከተል እና ያልተቋረጠና ተከታታይ ምዘና በማካሄድ ተማሪዎች ግንዛቤ፣ ችሎታ፣ አመለካከት እና በራስ መተማመንን እንዲጎናፀፉ በማድረግ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። ስለዚህ መምህራን የትምህርት አቅርቦት ችግርን ሊፈቱ የሚችሉ የመማር ዘዴዎችን በመጠቀም ትምህርትን ውጤታማ ማድረግ አለባቸው። መምህራን አስፈላጊ እና ትምህርትን ተጭባጭ ሊያደርጉ የሚችሉትን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና ግልጽ የሆነ የትምህርት ዕቅድ ለሁሉም የትምህርት ይዘቶች ማዘጋጀት አለባቸው። በተጨማሪም መምህራን በዚህ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ ተጨማሪ ገለጻዎችንና ከእያንዳንዱ ይዘቶች ጋር ተዛማችነት ያላቸውን ዋቢ መጽሐፍት በማንበብ እውቀታቸውንና ችሎታቸውን በማዳበር የትምህርቱን ዓላማ በማሳካት ውስጥ የራሳቸውን ድርሻ መወጣት አለባቸው። በሌላ በኩል የትምህርት ይዘቶችን መረዳት ላይ እርዳታ የሚፈልጉ ወይንም ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎችን በመለየት ማገዝ አለባቸው። መምህራን የትምህርት ይዘቶችን አላማዎች ወይንም ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸውን የትምህርት ብቃት (MLC) መሰረት በማድረግ መማር ማስተማሩን ማካሄድ ይኖርባቸዋል። እንዲሁም መምህራን በክፍል ውስጥ የሚሰጡትን ትምህርት ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ሊያገኙ ከሚችሉት ሐገር በቀል ዕውቀት (Indigenous Knowledge) ጋር በማዛመድ መስጠት አለባቸው።

# ምዕራፍ 1: ሳይንስን ግልጽ ማድረግ

ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ ብዛት....................................... 45

የምዕራፉ ትምህርት ውጤቶች:

በዚህ ምዕራፍ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ ተማሪዎች:

- ውጫዊ የሰው አካል ክፍሎችን ይለያሉ።
- የተለያዩ ውጫዊ የሰው አካል ክፍሎች ጥቅሞችን ይለያሉ።
- የስሜት አባለተ አካል ጥቅሞችን ይዘረዝራሉ።
- ልዩ ቁሶች ባላቸው ባህሪያት መሠረት የስሜት አባለተ አካላቸውን በመጠቀም ልዩ ቁሶችን ይለያሉ።
- የብርሃን ምንጮን ይናገራሉ

### መግብያ

ይህ ምዕራፍ የተለያዩ ሦስት ዋና ዋና ርዕሶችን በውስጡ ይዟል። የመጀመሪያው ሪዕስ የሰው ውጫዊ አካል ክፍሎችና የስሜት አባለተ አካላት ናቸው። በዚህ ርዕስ ውስጥ ተማሪዎች የውጫዊ አካል ክፍሎች እና የስሜት አባለተ አካላትና ጥቅማቸውን በመለየት በተግባር ያሳያሉ።

ሁለተኛው ርዕስ ልዩ ቁሶችን ስለ መለየት ነው። በዚህ ሪዕስ ውስጥ ተማሪዎች የስሜት አባላት አካላታቸውን በመጠቀም ልዩ ቁሶችን በመለየት ይናገራሉ።

ሶስተኛው ርዕስ የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጮን መለየት ላይ ያቶኩራል። በተጨማሪም ምዕራፉ የግንዛቤ ጥያቄዎችን እና ተማሪዎች የሚሳተፉበት ተግባራትን የያዘ ነው። ስለዚህ መምህራን ተማሪዎች በመፅሐፉ ውስጥ ያሉትን የግንዛቤ ጥያቄዎችን እና የተግባር ሥራ ላይ እንዲሳተፉ ማብረታታት አለባችው።

## 1.1 የሰውነታችን ውጫዊ አካል ክፍሎችና የስሜት አባለ አካላቶቻችን

ለዚህ የትምህሪት ይዘት የተሰጠ የክፍሌ ጊዜ ብዛት----------------------15

የዚህ ርዕስ ትምህርት ውጤቶች ፡

በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ ተማርው/ዋ

- የውጫዊ አካል ክፍሎችና የስሜት አካል አባላት ጥቅሞችን ይናገራል/ትናገራለች ።

- የውጫዊ አካል ክፍሎችና የስሜት አካል አባላት ጥቅሞችን በተግባር ያሳያል/ታሳያለች።

## ዋና ዋና ነጥቦች

ይህ ርዕስ በውጫዊ አካል ክፍሎች እና የስሜት አካላት ጥቅምን መለየት ላይ ያተኩራል። በዚህ ርዕስ ውስጥ የተማሪዎችን እውቀት፤ ክህሎት እና አመለካከት የሚያዳብሩ የተለያዩ የመማር ዘዴዎች እና የተማሪዎችን መማር ለመመዘን የሚያገለግሉ የምዘና ዘዴዎች ይቀርባሉ።

በዚህ የትምህርት ርዕስ የመማር ሂደት ተማሪዎችን በመፅሓፍ ውስጥ የተሰጡትን የተግባር ስራዎችን እና ጥያቄዎችን  በማሰራት ማሳተፍ ነው።

## ቅድሜ ዝግጅት

መጀመሪያ የዚህን ርዕሰ ትምህርት እቅድ ማዘጋጀት ነው። በመቀጠል በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ በተቀመጠው መሰረት የሰው ውጫዊ አካል ክፍሎች እና አምስቱን የሰሜት አባላተ አካል የሚያሳዩ ስዕሎችን ወይም ሞደሎችን ማዘጋጀት።

ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ መምህሩ በሰው ላይ ጉዳት የማያመጡ የተለያዩ ሽታ እና ጣዕም ያላቸውን ልዩ ቁሶች በማዘጋጀት ለመማር ማስተማር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው። እንደ ስኳር፤ ጨው፤ሎሚ፤ሽቶ እና የመሳሰሉትን ማዘጋጀት ይቻላል። እንደዚሁም የተለያዩ እንስሳት ድምፅ በመቅዳት እና በማሰማት በስሜት አካላቸው በመጠቀም እንድለዩ በማድረግ የስሜት አካላትን ጥቅም እንዲያውቁ ማድረግ።

## የመማር ማስተማር ዘዴ

በዚህ ትምህርት መግቢያ ላይ ተማሪዎች በአንደኛ ክፍል ትምህርታቸው ከተማሩት  ውስጥ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያላቸውን ግንዛቤ መለየት ያስፈልጋል። በመቀጠል የተማሪዎች የመማር ማስተማር ዘዴ የሚያግዙ እንደ ምልከታ፤ ቀላል ሙከራ ፤የቡድንና  የጥንድ ውይይትና ሌሎች ምቹ የሆኑ የመስተማር ዘዴዎችን  በመጠቀም  የመማር ማስተማሩን ሂደት ማሳካት ነው።

ተማሪዎች በግል ፣ በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው የውጫዊ አካል ክፍሎችን እና የስሜት አካል አባላትን ጥቅም ምን ያህል እንደሚያውቁ በቡድን በማወያየት እንዲናገሩ ማድረግ ነው። በተማሪዎች መልስ ላይ በመሞርኮዝ የውጫዊ አካል ክፍሎች ስዕሎችን ወይም ሞደሎችን በመጠቀም ጥቅማቸውን ማብራራት ነው። በተጨማሪም የስሜት አባላተ አካላታቸውን በመዝሙር መልክ እርስ በርሳቸው እንድዘሚሩ ማብረታታት። የስሜት አባላተ አካላቸውን

ሥራ በመፅሐፋቸው ላይ በተቀመጡ ስዕሎች መሰረት እንዲለማመዱ በማድረግ ግንዛቤያቸውን ማዳበር፡፡

ለምሳሌ የምላስን ጥቅም ለማወቅ የተዘጋጁትን እንደ ስኳር፤ ሎሚ እና ጨው እንድቀምሱ ማድረግ፡፡ የጆሮን ጥቅም ለማወቅ የተለያዩ የእንስሳት ድምፅ ማሰማት፡፡ ከተማሪዎች መካከል የተለያዩ የእንስሳትን ድምጽ ማስመሰል የሚችሉ ካሉ በፍቃደኝነት የውሻ፤ የድመት፣ የአህያ፤ የጅብ፤ የበግ ፣የከብት እና የመሳሰሉትን ድምፅ እንዲያሰሙ ማድረግ፡፡

**ተግባር** 1.1. በተማሪው መፅሐፍ ላይ ያለውን ስዕል ወይም ለዚህ ትምህርት ተብሎ በተዘጋጀው ስዕል ላይ ተማሪዎች በቡድን በመወያየት እንዲናገሩ ማድረግ

**ተግባር** 1.2 የተለያዩ እንስሳትን ድምፅ የድመት፣ ጦጣ፣ ዝንጀሮ፣ ላም ፣ ውሻ፣ ጅብ እና የአእዋፋትን በማስመሰል ተማሪዎች በአከባቢያቸው የሚገኙትን የእንስሳት ድምፅን በፍላጎታቸው እንዲያሰሙ ማድረግ፡፡

የስኳር፤ ማር፤ ሎሚ፤ ጨው፤ ሽንኮራ አገዳ፤ ብርቱካን እና ውሀ የመሳሰሉትን ልዩ ቁሶችን ጣዕም እንዲለዩ ማድረግ፡፡ የእነዚህን ልዩ ቁሶች ጣዕም በምን እንደሚለዩ በመጠየቅ ግንዛቤያቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ምላስ የስሜት አባለ አካል ሆኖ የልዩ ቁሶችን ጣዕም የሚንለይበት መሆኑን ማስገንዘብ ነው፡፡ የልዩ ቁሶች ጣዕም ጣፋጭ፤ መራራ፤ ኮምጣጣ እና ጨዋማ መሆናቸውን አስገንዘባቸው፡፡

**ማሳሰቢያ፡** ሁሉንም ለዩ ቁሶች መቅመስ ጉዳት ሊያስከትለ ስለሚችል ተማሪዎች የማያውቁትን እንዳይቀምሱ ማስጠንቀቅ ያስፈልጋል ፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ ማገዝ

በዚህ ርዕስ ሥር የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ የሚያዳብሩ የሰውን ውጫዊ አካል ክፍሎችን የሚያሳዩ እንደ ስዕልና ሞዴል ከአከባቢያቸው ከሚገኙት ነገሮች ከጣውላ እና ከግራፍ ወረቀት መስራት እንድችሉ ማብረታታት አስፈላጊ ነው፡፡

## የምዘና ዘዴዎች

በመግቢያ ላይ መምህሩ/ርቷ ተማሪዎች ስለ የሰው ልጅ ውጫዊ አካል ክፍሎች እና የስሜት አባላተ አካላት ጥቅሞች የሚያውቁትን እንዲናገሩ በመጠየቅ ግንዛቤያቸውን መለየት ነው፡፡ ከዚያም በሂደት ስለ የሰው ውጫዊ አካል ክፍሎች እና የስሜት አባላተ አካላት ጥቅሞች ላይ

ማብራሪያ እንድሰጡ በማድረግ እየመዘኑ መሄድ። በመጨረሻም እያንዳንዱ ተማሪ አነስተኛው የመማር ብቃት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ በግል ወይም በጥንድ ወይም በቡድን በመሆን ጥያቄዎች እና ተግባራትን እድሰሩ በመስጠት መመዘን። እንዲሁም ተማሪዎች በቡድን ሲወያዩ መምህሩ ተማሪዎችን ተዘዋውሮ በመመልከት ድጋፍ መስጠት። ተማሪዎች አነስተኛ የመማር ብቃት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ተግባራትን በማዘጋጀት ስራቸውን በየግዜው በመመዘን ማስታወሻ በመያዝ እና ግብረ መልስ በመስጠት እያበረታቱ መምራት።

## የተግባር መልሶች

**ተግባር 1.1**

1. ፀጉር
2. ራስ
3. ጆሮ
4. አፍንጫ
5. ደረት
6. አንገት
7. እጅ
8. ሆድ
9. ጉልበት
10. እግር
11. የእግር ጣት

**ተግባር 1.2 ድምፅ**

ፍዬል -መ መ መ

ውሻ-ው ው ው

ድመት —ሚያው ሚያው

ዶሮ- ኩኩሉ ኩኩሉ

ፈረስ-ሂ ምም

## 1.2 ልዩ ቁሶችን መለየት

ለዚህ የትምህሪት ይዘት የተሰጠ የክፍሌ ጊዜ ብዛት--------------------- 15

የዚህ ርዕስ ትምህርት ውጤቶች ፡

በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ ተማርው/ዋ

- ባህሪያቸው ላይ በመመስረትና የስሜት አካላትን በመጠቀም ልዩቁሶችን ይለያል/ትለያለች ።

## ዋና ዋና ነጥቦች

ተማሪዎች በስሜት አካላቸው መለየት የሚችሉት የልዩቁሶች አካላዊ ባህሪይ እንደ ቀለም፤ ጣዕም፤ ሽታ፤ ቅርፅ፤ መጠንና ጥንካሬ መሆናቸውን ማስገንዘብ።

ይህን ርዕስ ለማስተማር የተማሪዎችን እውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት የሚያዳብሩ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች እና ለተማሪዎች መማር የሚያግዙ የምዘና ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው።

በዚህ ርዕስ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በተማሪ መፅሓፍ ውስጥ የተሰጠውን ጥያቄዎች እና ተግባራት መልስ በመስጠት እና በመስራት ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማበረታታት ነው።

## ቅድመ ዝግጅት

ከሁሉም በፊት የትምህርቱን እቅድ ማዘጋጀት። ይህን ትምህርት በተግባር መደገፍ አስፈላጊ ስለሆነ በአከባቢያችሁ የሚገኙ የተለያየ አካላዊ ባህሪያት ያሉዋቸውን እንደ ሎሚ፣ ስከኳር፣ ማር፣ ጨው፣ ሽቶ፣ ጠንካራ ድንጋይ እና ለስለሳ ድንጋይ የመሳሰሉትን ልዩ ቁሶች አስቀድሞ ማዘጋጀት። እንዲሁም የተለያዩ ቅርፅና መጠን ያላቸውን እንደ ብሎኬት፣ ኳስ፣ ብርጭቆ፣ ጠረጰዛ እና ድንጋይ ማዘጋጀት።

## የመማር ማስተማር ዘዴ

በትምህርቱ መግብያ ላይ ለዚህ ትምህርት የተዘጋጁትን ልዩ ቁሶች በማስጎብኘት ተማሪዎች የእነዝህን ልዩ ቁሶች አካላዊ ባህሪይ ላይ በግል በማሰብ እና በጥንድ ወይም በቡድን ተወያይተው እንዲናገሩ በማድረግ ትምህረቱን መጀመር። ተማሪዎች በሚሰጡት መልስ ላይ በመመርኮዝ የልዩ ቁሶች አካላዊ ባህሪይ እንደ ቀለም፣ ሽታ፣ ቅርፅ፣ ጥንካሬ እና የመሳሰሉትን በየትኛው የስሜት አባላተ አካላቸው መለየት እንደሚችሉ ማሳየት አስፈላጊ ነው። መምህራን ወደ ሚቀጥለው ርዕስ ከማለፋቸው በፊት እያንዳንዱ ተማሪ በተማሪ መፅሐፍ ላይ የተሰጠውን የልዩ ቁሶችን አካላዊ ባህሪይ ለይተው ማወቃቸውንና እንዝህ የልዩ ቁሶች ባህሪያትን በመጠቀም ልዩ ቁሶችን እንዴት መለየት እንደሚቻል መረዳታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

**ተግባር 1.3** ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን በመሆን በተግባር 1.3 ላይ የተዘረዘሩትን የልዩ ቁሶችን ቀለም፣ ሽታ፣ ቅርፅ፣ ጣዕም እና መጠንን በየትኛው የስሜት አካላት መለየት እንደሚቻል ተወያየተው መብራሪያ እንድሰጡ ማድረግ።

**ተግባር 1..4** ተማሪዎች በቡድን ከተወያዩበት በኃላ በአከባብያቸው ከሚገኙት ልዩ ቁሶች ውስጥ ጣፋጭነት፣ መራራነት፣ ኮምጣጣነት እና ጨዋማነት ያላቸው ልዩ ቁሶችን ለይተው እንዲዘረዝሩ ማድረግ

**ተግባር 1.5** ተማሪዎች በየግላቸው በመሆን በዚህ ተግባር ውስጥ የተዘረዘሩትን ብርጭቆ፣ ድንጋይ፣ ብረት፣ ሶፍት፣ ፕላስትክ እና ጎማ በጥንካሬያቸው እንድመድቡ በማድረግ በመጨረሻ ላይ ግብረ መልስ መስጠት ነው፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ ማድረግ

በዚህ ርዕስ ሥር ተማሪዎች የልዩ ቁሶች ባህሪያትን በመጠቀም በአከባብያቸው የሚገኙትን ልዩ ቁሶችን መለየት ተግባር ውስጥ የምልከታ፣ የምደባ፤ የሙከራና ትርጉም መስጠት ክህሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡

## የምዘና ዘዴዎች

እያንዳንዱ ተማሪ የልዩ ቁሶች ባህሪያት ለይ በመመሥረት ልዩ ቁሶችን መለየት መቻሉን/መቻሉዋን በመጠየቅ ግንዛቤውን/ዋን እየገመገሙ መሄድ ነው፡፡ በተማሪዎች መፅሐፍ ውስጥ የተሰጡትን ሥራዎች ሁሉ በግል እና በቡድን እንድሰሩ በማድረግ ግንዛቤያቸው መዳበሩንና ችሎታቸውን እየገመገሙ ድጋፍ ማድረግ እና ግብረ መልስ መስጠት ነው፡፡

## የተግባር መልስ

**ተግባር 1.3**

1.

ቀለም - በዓይን

ቅርፅ - በዓይን፤ በእጅ

መጠን - በዓይን

ጣዕም - በምላስ

ሽታ - በአፍንጫ

2. ተማሪዎች በሚሰጡት መልስ ይወሰናል

**ተግባር 1.4**

1. **መራራ**-ግራዋ፤ የኮሶ እንጨት
2. **ጣፋጭ**- ማር፤ስኳር፤የሸንኮራ አገዳ
3. **ኮምጣጣ**- ሎሚ፤ ብርቱካን፤ ኮምጣጣ

**ተግባር 1.5**

**ጠንካራ-**ብረት፣ ብርጭቆ

**ለስለሳ-** ፕላስትክ፣ ጎማ፣ ሶፍት

## 1.3 የብርሃን ምንጮች

ለዚህ የትምህሪት ይዘት የተሰጠ የክፍሌ ጊዜ ብዛት----------------------15

የዚህ ርዕስ ትምህርት ውጤቶች ፡

በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ ተማሪው/ዋ

- የብርሃን ምንጮችን ይናገራል/ትናገራለች ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ርዕስ ትምህርት ሥር ተማሪዎች እንደ ጸሐይ፣ ከዋክብት፣ ኤሌክትርክ፣ ሻማ፣ ኩራዝ፣ እሳት የመሳሰሉት ነገሮች የተፈጥሮ ወይም የሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጭ መሆናቸውን ይማራሉ፡፡

ይህን ርዕስ ለማስተማር የተማሪዎችን እውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት የሚያዳብሩ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች እና ለተማሪዎች የሚያገለግሉ ሚዘናዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

በዚህ የመማር ማስተማር ሂዴት ውስጥ በተማሪ መፅሐፍ ውስጥ የተሰጡትን ጥያቄዎች እና ተግባራት መልስ በመስጠት እና በመስራት ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማብረታታት ነው፡፡

## ቅደመ ዘግጅት

መምህሩ/ሯ ለእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት አለበት/ባት፡፡ የብርሃን ምንጭ የሆኑትን እንደ ባትሪ እና ሻማ አዘጋጅ/ጂ፡፡ የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጭን የሚያሳዩ የተለያዩ ስዕሎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ተማሪዎች በብርሃን ላይ ያላቸውን እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር፡፡ ለምሳሌ ብርሃን ምን እንደ ሆነ መጠየቅ፡፡ ተማሪዎች በግል፡ በጥንድ እና በቡድን በመሆን የብርሃን ምንጭ እንድዘረዝሩ ማድረግ፡፡ የብርሃን ምንጭ የሆኑትን የተለያዩ ቁሶችን ወደ ክፍል በማምጣት

ትምህርቱ ለተማሪዎች ግልፅ እንድሆን ማድረግ አስፈልጊ ነው፡፡ እንድሁም ተማሪዎች በግልና በጥንድ በመሆን ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮን የብርሃን ምንጮችን በመለየት እንድዘረዝሩና እንዲያብራሩ ማድረግ ነው፡፡ የብርሃን ምንጮችን በተማሪ መፅሃፍ ላይ እንደተብራራው በመወያየት እንድዘረዝሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማገዝ

ተማሪዎች የምልከታ፤ ያምደባ እና የሙከራ ክህሎታቸውን እንድያዳብሩ ማግዝ ነው፡፡

## የምዘና ዘዴዎች

በመጀመሪያ ተማሪዎች ስለ ብርሃን ያላቸውን ዕውቀት ጠይቆ በመዳሰስ ችሎታቸውን መመዘን ነው፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች በአከባብያቸው የሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ የብርሃን ምንጮችን እና ባህሪያቸውን እንዲናገሩ በመጠየቅ ሙከራ እና የተለያዩ ተግባራትን እንድሰሩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ተማሪዎች የሚሰጡትን መልስ በመከታተል ግብረ መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ተማሪዎችን ማግኘት የሚገባቸውን ብቃት ለማረጋገጥ የተለያዩ ተግባራትን በማዘጋጀት እና ሥራቸውን በየግዘው በመመዘን ማስታወሻ እየያዙ መሄድ እና ግብረ መልስ በመስጠት እያብረታቱ መምራት ነው፡፡

የ 1.6 ተግባር መልስ

የተፈጥሮ የብርሃን ምንጮች፡ ፀሓይ፣ ክዋክብት

የሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጮች፡ ሻም፣ ኩራዝ፣ ባትሪ፣ አምፑልና የመሳሰሉት

## የምዕራፉ 2 መልመጃ

**ሀ. እውነት ወይም ውሸት በማለት መልስ**

1. እውነት
2. ውሸት
3. እውነት
4. እውነት

**ለ. አዛምድ.**

1. ሐ
2. ሠ
3. መ
4. ለ
5. ሀ

**ሐ. ምርጫ**

1. መ
2. ሐ
3. ሐ
4. ሐ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ

1. **አንገት**- ራስን ደግፎ ለመያዝ ይረዳል
   **እግር**-እንድንቆምበት እና እንድንሄድበት የረዳናል
2. የተፈጥሮ የብርሃን ምንጮች ለምሳሌ ፀሐይ፤ከዋክብት፤ትሎች እና የመሳሰሉት ናቸው።
   ሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጮ ደግሞ ሻማ፤ እሳት፤አምፑል እና የመሳሰሉት ናቸው።፡

# ምዕራፍ 2 ፡ መገኛ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት**: 34

**የምዕራፉ ትምህርት ውጤት**

**በዝህ ምዕራፍ ትምህርት ማጠቃላያ ላይ ተማሪዎች**

- የመገኛን ምንነት ይገልጻሉ፡፡
- የአንጻራዊ መገኛን ምንነት ግልጽ ያደረጋሉ፡፡
- የወረዳቸውን አንጻራዊ መገኛን ያሳያሉ፡፡
- የወረዳቸውን መገኛ ከአጎራባች ወረዳዎች ጋር በማነጻጸር ያሳያሉ፡፡
- በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን ቀበሌዎች ሥም በመናገር መገኛቸውን በቀላል ካርታ ላይ ያሳያሉ፡
- ወረዳቸውን የሚያዋስኑ ወረዳዎችን ስም ይጠራሉ፡፡

## የምዕራፉ መግቢያ

በአንደኛ ክፍል የአከባቢ ሳይንስ ምዕራፍ አንድ ውስጥ እንደ ግራ፣ ቀኝ፣ ኋላና ፊት ያሉትን አቅጣጫዎች እንዲሁም ስለቀበሌያቸው መገኛ አስመልክቶ መሰረታዊ ዕውቀት አግኝተዋል፡፡ ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ በአንደኛ ክፍል ውስጥ የተማሩትን እንደ መነሻ በመጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ይሄውም የቀበሌያቸውን አቅጣጫና መገኛ መወቅ ወሳኝ ነው፡፡ የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ትኩረት ደግሞ የመገኛ ምንነት፣ አንፃራዊ መገኛ፣ የወረዳችን አንፃራዊ መገኛ፣ በወረዳችን ውስጥ የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎችና ቀበሌዎች ስምና አንፃራዊ መገኛ የሚሉ ርዕሶችን ያጠቃልላል፡፡

ስለዚህ፣ በዚህ ምዕርፍ ውስጥ ተማሪዎች እንዲጎናጸፉት የሚፈለገውን የመማር ብቃት እውን ለማድረግ መምህሩ/ርቷ ከፍተኛ ድርሻ አለው/ላት፡፡ ስለሆነም ይእያንዳንዱን ረዕስ ትምህርት ተጨባጭ ለማድረግ እና ተማሪዎች ስለወረዳቸው እና በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎችን በትክክል እንዲረዱ ለማድርግ መምህሩ/ርቷ የተለያዩ ካረታና ስዕሎችን መጠቀም ይጠበቅበታል/ባታል፡፡ ተማሪዎች ሊረዱ የሚገቡ የመማር ብቃትን ለመገምገም የሚረዱ የተለያዩ የተግባር ጥያቄዎች፤ መልመጃዎች እና የግንዛቤ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው ፡፡

## የምዕራፉ ዋና ዋና ነጥቦች

ተማሪዎች በአንደኛ ክፍል ትምህርት ውስጥ የተማሩትን ትምህርት መሰረት በማድረግ ስለመገኛ እና አንፃራዊ መገኛ እንደዚሁም ስለ ወረዳቸው መገኛ እና ጎረቤት ወረዳዎች እንዲናገሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች ሊረዱ የሚገባቸውን የመማር ብቃትን እንዲያገኙ ማድረግ ከመምህራን ይጠበቃል፡፡ ዋና ዋና የሆኑ የአቅጣጫ አመልካቾች ለምሳሌ ሰሜን፤ ደቡብ፤ ምስራቅ እና ምዕራብ በመጠቀም የወረዳቸውን/የከተማ አስተዳደራቸውን አንፃራዊ መገኛ፤ በወረዳቸው/በከተማ አስተዳደራቸው ወስጥ የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎችን ተማሪዎች እንዲለዩ ማድረግ የዚህ ምዕራፍ ዋና ዋና ነጥቦች ናቸው፡፡ የወረዳቸውን ተዋቂ ቦታዎች እና በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙ ቀበሌዎችን በወረዳቸው ካርታ ለይ በትክክል ማሳየት መቻል ከእያንዳንዱ ተማሪ የሚጠበቀው ሌላኛው ዝቅተኛው የመማር ብቃት ነው፡፡

## 2.1 የመገኛ ምንነት

**ለዚህ የትምህርት ይዘት የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት 2**

**የዚህ ርዕስ የመማር ውጤት**

**በዚህ ርዕስ ትምህርት ሂደትና ማጠቃሊያ ላይ ተማሪው/ዋ**

- የመገኛ ምንነትን ይገልፃል/ትገልፃለች፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

የመገኛ ምንነት የሚለውን ርዕስ ከተማሩ በኃላ ተማሪዎች “የመገኛ መንነትን `ይገልፃሉ” የሚለውን አነስተኛውን የመማር ብቃትን “ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ትምህርት ዓላማ ግቡን እንድመታ ለማድረግ ተማሪዎች መፅሓፍ ላይ ያለውን ስዕል 1.1 በማንሳት በአራቱም አቅጣጫ በስዕሉ ላይ የተቀመጡትን ነገሮች ግልፅ ማድረግ ከማምህሩ/ርቷ ይጠበቃል፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

በመማሪያ መፅሐፍ ላይ ያለውን ስዕል አሳድገው በማንሳት ለሁሉም ተማሪዎች በሚታይ ቦታ ላይ መስቀል ያስፈልጋል፡፡ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ሲዘጋጅ ተማሪዎችን በሚያሳትፍ እና ማግኘት የሚገባቸውን የመማር ብቃትን በሚያረጋግጥ መልኩ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

በአንደኛ ክፍል ውስጥ የተማሩትን  የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለ መገኛ ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ  ማረጋገጥ የዚህ ርዕስ  ትምህርት ተቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ ተማሪው/ዋ ለመማሩ/ረዋ ሀላፊነቱን እንድወስድ/ትወስድ ተማሪዎችን ያማከለ የትምህርት ሂደት ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡

በዚሁ መሰረት ተማሪዎች በስዕል 2.1. ላይ ያሉትን የነገሮች መገኛ መጀመሪያ በግላቸው ከዚያም ሁለት ሁለት በመሆን በመጨረሻ በቡድን በመሆን ከተወያዩ በኃላ ለክፍል እንድያቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያለውን ስዕል 1.1. በማንሳት ቀኝ፣ ግራ፣ ኃላና ፍት በማለት አቅጣጫዎችን እንድለዩ በማበረታትና በማነቃቃት የተማሪዎችን ተሳትፎ በመመዝገብ ግብረ መልስ መስጠት ጥሩ ዘዴ ነው፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ መርዳት

በዚህ ረዕስ ስር ተማሪዎች በአንደኛ ክፍል  ውስጥ የተማሩትን መነሻ በማድረግ ስለ መገኛ ምንነት በጥልቀት በጥልቀት ይማራሉ፡፡ በዚህ ትምህርት ውስጥ ከተማሪዎች የሚጠበቀው የፈጠራ ችሎታ በአከባቢያቸው የሚገኙ ነገሮች የነገሮችን መገኛ የሚያሳይ ካርታ መስራት ነው፡፡ ስለዚህ መምህራን እንደዚህ ዓይነት የፈጠራ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎችን በመለየት ችሎታቸውን እንድያዳብሩ እገዛ እንድያደርጉላችው ያስፈልጋል፡፡

## የምዘና ዘዴዎች

ተማሪዎች መጎናፀፍ የሚገባቸውን ዝቅተኛውን የመማር ብቃትን መጎናፀፋችውን ለማረጋገጥ በመማሪያ መፅሀፍ ከስዕል 2.1 ጋር የተሰጡትን ጥያቄዎች እያንዳንዱን መስራታችውን ለማረጋገጥ ምልከታና ክትትል ማድረግ ከመምህሩ/ርቷ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ ምዘና በኃላ ከአፈፃፀም ደረጃችው ጋር የሚመጣጠን ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

## የግንዛቤ ጥያቄዎች መልስ

ከልጅቷ በስተ ግራ በኩል የሚገኘው መኪና ነው፡፡  በስተ ቀኝ በኩል የሚገኘው ደግሞ ቤት ነው፡፡ ከቆመችው ልጀ  ፊት ለፊት ላይ የሚገኙት ፊየሎች ሲሆኑ፤ ከእሱዋ  ከበስተ ኃላ የሚገኘው ደግሞ ዛፍ ነው፡፡

## 2.2 የአንፃራዊ መገኛ ምንነት

**ለዚህ የትምህርት ይዘት የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ------- 4**

**የዚህ ርዕስ የመማር ውጤቶች**

በዚህ ረዕስ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ ተማሪው/ዋ፡

- የአንፃራዊ መገኛ ምንነትን ይገልፃል/ትገልፃለች፡፡

# ዋና ዋና ነጥቦች

የአንፃራዊ መገኛ ምንነት እና አንፃራዊ መገኛ የሚገለፅበትን አራቱን አቅጣጫዎች ማለትም ሰሜን፤ደቡብ፤ ምስራቅ እና ምዕራብ ለይተው ማሳየት የዚህ ክፍል ዋና ትኩረት ነው፡፡ በተጨማሪም እነዚህን ዋና ዋና አቅጣጫዎችን በመጠቀም የተለያዩ ቦታዎችን መገኛ መግለፅ መቻል ከተማሪዎች የሚጠበቅ ነው፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

አራቱን ዋና ዋና አቅጣጫዎችን የሚያሳይ አቅጣጫ ጠቋሚ ኮምፓስና አራቱን አቅጣጫዎች የሚያሳይ የሰው ሞዴል ወይም ስዕል በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በስዕል 1.2 ላይ በተቀመጠው መሰረት በትልቁ ተማሪዎችን በሚስብ መልኩ ስሎ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ተማሪ ተኮር የሆነ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት የመምህሩ/ርቷ ቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ እንድዚሁም የርዕሱን ዝቅተኛውን የመማር ብቃት ለማሳከት የሚያግዙ የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን በትክክል ማዘጋጀት ከመምህራን ይጠበቃል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ተማሪዎች ሊጎናፀፉት የሚገባቸውን ዝቅተኛውን የመማር ብቃትን እንዲጎናጸፉ ጥንድ ጥንድ በመሆን የዋና ዋና አቅጣጫዎችን ምንነት ገልፀው በተግባርና በጫወታ መልክ እንድያሳዩ መምራት ከመምህራን ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በተግባር 2.2 ውስጥ በተሰጠው መሰረት ተማሪዎች አንድ በአንድ ተነስተው ቤታቸው ከትምህርት ቤታቸው በየትኛው አቅጣጫ እንደሚገኝ እንዲናገሩና እንድያሳዩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን ማጠናከር ነው፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ ማገዝ

በዚህ ርዕስ ውስጥ ተማሪዎች ሊያዳብሩ የሚገባቸው ፈጠራ አራቱን አቅጣጫዎችን የሚያሳይ ሞዴል በአከባቢ ከሚገኙ ነገሮች እንዲሰሩ ማበረታታት ነው፡፡

## የምዘና ዘዴዎች

እያንዳንዱ ተማሪ በተግባር 2.1 ላይ የሚያደርገውን ተሳትፎ መመልከትና ማስታወሻ በመያዝ ለተማሪዎቹ ግብረ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ መምህራን ማስታወሻቸውን በማየት ለተማሪዎች የፅሁፍ ግብረ መልስ ቢሰጡ መልካም ነው፡፡ በተጨማሪም ከመማሪያ መፅሀፍ ውጪ ተጨማሪ መልመጃዎችን በማዘጋጀት ለተማሪዎች መስጠት ያስፈልጋል፡፡ የተግባር 2.1. መልስ በትምህርት ቤታቸው አቀማመጥ መሰረት የሚመለስ ስለሆነ አንድ ዓይነት ሊሆን አይችልም፡፡

# 2.3 የወረዳችን አንፃራዊ መገኛ

**ለዚህ የትምህርት ይዘት የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ---------------- 8**

የዚህ ርዕስ የመማር ውጤት

በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጣቃላያ ላይ ተማሪው/ዋ፡

- የወረዳውን/ዋን መገኛ ከአጎራባች ወረዳዎች ጋር በማነጻጸር ያሳያል/ታሳያለች፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

የዚህ ርዕስ ትምህርት ዋና ነጥብ ተማሪዎች የወረዳቸውን መገኛ ከጎረቤት ወረዳዎች ጋር በማነፃፀር ማሳየትና መናገር እንዲሁም የወረዳቸውን ጎረቤት ወረዳዎች መገኛ አቅጣጫዎችን በካርታ ላይ መሳየትና መናገር ነው፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

በስዕል 2.3 ላይ የተቀመጠውን ካርታ እና የወረዳቸውን የጎረቤት ወረዳዎችሁሉ የሚያሳይ ካርታ በትልቁ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም የተማሪዎችን ተግባር ብውስጡ ያካተተና አሳታፊ የሆነ የትምህርት ዕቅድ እና ርዕሱ የሚፈልገውን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በትክክል ማዘጋጀት ከመምህሩ/ዋ ይጠበቃል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኃላ የሚፈለገውን ዝቅተኛውን የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ በስዕል 2.3 ላይ ያለውን ቀላል ካርታ በትልቁ በማንሳት ጥንድ ጥንድ ሆነው ከተወያዩ በኃላ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

እንደዚሁም ተማሪዎች የወረዳቸውን እና የጎረቤት ወረዳዎችን ቀላል ካርታ በመመልከት የወረዳቸውንና የጎረቤት ወረዳቸውን አንጻራዊ መገኛ ለይተው እንድያስዩ ለማድረግ ማበራታታትና መርዳት አስፈላጊ ነው። መምህራን በመማሪያ መጽሓፍ ላይ ከተቀመጠው ውጪ ሌሎች መልመጃዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎች መጀመሪያ በግላቸው፤ በመቀጠል በቡድን በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ መልካም ነው።

## የምዘና ዘዴዎች

ተማሪዎች በዚህ ርዕስ ላይ የተቀመጠውን የመማር ብቃት ላይ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ በተግባር 2.3 ውስጥ የተሰጡትን ጥያቄዎች ማሰራት ያስፈልጋል። እያንዳንዱ ተማሪ በመጽሃፉ ውስጥ የተሰጠውን ተግባር መስራታቸውን ለማረጋገጥ ደብተራቸውን ማረም ያስፈልጋል። መምህራን የተማሪዎችን ተሳትፎ በመመልከት እና በመመዝገብ የእያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎ በመገምገም ግብረ መልስ መስጠት አለባቸው።

የተግባር 1.3 መልስ እንደ ወረዳቸው እና እንደ ጎረቤት ወረዳቸው ተጨባጭ ሁኔታ የሚመለስ ስለሆነ መልሱ አንድ ልሆን አይችልም።

# 2.4 በወረዳችን የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎች

**ለዚህ ትምህርት ይዘት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት ---------------- 10**

የዚህ ርዕስ የመማር ውጤት

በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጣቃላያ ላይ ተማሪው/ዋ፡

- በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን ታዋቂ ቦታዎችን በወረዳው ካርታ ላይ ያሳያል/ታሳያለች ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

የዚህ ርዕስ ትምህርት ዋና ነጥብ ተማሪዎች በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን ተዋቂ ቦታዎች በወራዳው ካርታ ላይ ማሳየት መቻል ነው፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

ተማሪዎች የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ አድርገው ለማስተማር በቅድሚያ የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ማዘጋጀት አለባቸው። ከነዚህም የትምህርት የመርጃ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን ታዋቂ ቦታዎችን የሚያሳይ የወረዳው ካርታ ነው፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ተማሪዎች በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎችን እንዲለዩ የተለያዩ የቡድን የተግባር ሥራዎችን ወይም ፕሮጀክቶችን እንዲሰሩ መስጠት አስፈላጊ ነው። አስቀድሞ በተዘጋጀ የወረዳቸውን ካርታ በመጠቀም በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን ተዋቂ ቦታዎች በከርታው ላይ ማሳየት እንዲችሉ ማድረግ ነው። ተማሪዎች በካርታ አጠቃቀም ላይ ያላቸው ብቃት በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ መምህሩ/ዋ አስቀድሞ/ማ ምቹ የመማር ሁኔታዎችን መፍጠር አለበት/ባት።

## የምዘና ዘዴዎች

እያንዳንዱ ተማሪ በዚህ ርዕስ ሥር የተሰጠውን ተግባር መስራቱን/ቷን መከታተል፣ ማበረታታት እና የእያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎ በመመዝገብ ግብረ መልስ መስጠት ያስፈልጋል። በዚህ ደረጃ ላይ ተማሪዎች በወርዳቸው ውስጥ የሚገኙትን ታዋቂ ቦታዎች በወረዳው ካርታ ላይ ማሳየት ከቻሉ በቂ ነው። ስለዚህ ይህንን ማድረግ መቻላቸውን መከታታል ነው።

# 2.5 የወረዳችን ቀበሌዎች መገኛና ስማቸው

**ለዚህ ትምህርት ይዘት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት ---------------- 10**

የዚህ ርዕስ የመማር ውጤት፡

በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጣቃላያ ላይ ተማሪው/ዋ፡

- የወረዳቸውን ቀበሌዎች ስምና መገኛ በወረዳቸው ካርታ ላይ ያሳያል/ ታሳያለች።

## ዋና ዋና ነጥቦች

የዚህ ርዕስ ትምህርት ዋና ነጥብ ተማሪዎች በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን ቀበሌዎች ስምና መገኛቸውን በወረዳው ካርታ ላይ ማሳየት እንዲችሉ ማድረግ ነው።

## ቅድመ ዝግጅት

በቅድሚያ በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙ ቀበሌዎችን የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት ከመምህራን ይጠበቃል። ከላይ በተቀመጠው የትምህርት ግብ መሰረት የየዕለቱን የትምህርት ዕቅድ በአግባቡ ማዛገጀት ነው።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

“የወረዳችን ቀበሌዎች መገኛና ስማቸው” የሚለውን ርዕስ ለማስተማር በተማሪዎች መፅሓፍ ውስጥ በተቀመጠው ካርታ ላይ በሀ፣ ለ፣ሐ፣መና ሠ ፊደላት የተሰጡትን ቀበሌዎች ተማሪዎች በመጀመሪያ በግል እንዲያጠኑ ከተደረገ በኃላ የተረዱትን ሁለት ሁለት ሆነው እንዲወያዩ በማድረግ ማበረታት ነው። በተጨማሪም ሁሉም ተማሪዎች ተራ በተራ የካርታ ላይ የቀበሌዎችን መገኛ እንዲያሳዩ ማድረግ ያስፈልጋል። እንዲሁም የተሰጠውን ተግባር እያንዳንዳቸው ሰርተው እንድያቀርቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

## የምዘና ዘዴዎች

እያንዳንዱ ተማሪ በዚህ ርዕስ ስር የተሰጠውን ተግባር መስራታቸውን መከታተል፣ ማበረታታት እና የእያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎ በመመዝገብ ባገኙት ውጤት ላይ ግብረ መልስ መስጠት ያስፈልጋል።

### የምዕራፍ አንድ የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ

**ሀ. እውነት/ሀሰት**

1. ሀሰት 2. እውነት 3. እውነት 4. ሀሰት 5. እውነት

**ለ. የምርጫ ጥያቄዎች መልስ**

1. ለ 2. ሀ 3.መ 4. ሀ

# ምዕራፍ 3: የተፈጥሮ አከባቢ

ለዚህ የትምህርት ይዘት የተመደበው የክፍሌ ጊዜ ብዛት---------------------- 45

**የምዕራፉ የመማር ውጠቶች፡**

**በዚህ ምዕራፍ ትምህርት ማጠቃላያ ላይ ተማሪዎች**

- የአየር ጠባይ ምሳሌን ይሰጣሉ፣
- የአየር ጠባይ በየቀኑ የሚለዋወጥ የአየር ሁኔታ ነው በማለት ፍቺውን ይሰጣሉ፣
- የአየር ንብረትን የረጅም ግዜ አማካይ የአየር ሁኔታ ነው በማለት ይተረጉማሉ፣
- የአየር ንብረት በአኗኗራቸው ላይ እንዴት ተፅዕኖ እንደሚያደርስ ይገልፃሉ፣
- በአከባብያቸው በብዛት የሚገኙትን ዕፅዋት ይለያሉ፣
- ለዕፅዋት እድገት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ይጠቁማሉ፣
- ዕፅዋት ያላቸውን የተለያዩ ጥቅምችን ይለያሉ፣
- ለእንስሳት ኑሮ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ይዘረዝራሉ፣
- እንስሳትን የጀርባ አጥንት ያላቸውና የሌላቸው በማለት በስማቸው በምድባቸው ይመድባሉ፣
- በአከባቢያቸው ተመልሰውና ወደ አድስነት በመቀየር ጥቅም ላይ መዋል የሚችሉ ቁሶችን ይለያሉ።

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በአየር ጠባይ እና በአየር ንብረት መካከል ያለው ልዩነት ይታያል። የአየር ጠባይ የአየር መለዋወጥ ስሆን የአየር ንብረት ደግሞ በአንድ በተወሰነ አከባብ አማካይ የአየር ሁነታ በተደጋጋም ለረዥም ጊዜ የሚከሰት መሆኑን ይማራሉ።

ሎላኛው የዚህ ምዕራፍ ዋና ርዕስ ስለ ዕፅዋት ነው። በዚህ ሪዕስ ስር ፀሐይ፣ ውሃ እና አየር ለዕፅዋት እድገት አስፈላጊ መሆናቸውን ተማሪዎች ሙከራ ወይም የተለያዩ ተግባራትን በመስራት እንድያረጋግጡ ማድረግ ነው። የወረዳቸውን ዕፅዋት በመለየት በተለያዩ ምድቦች መመደብ እንድችሉ መምራት ነው። እፅዋት ለምግብነት፣ ለአልባሳት፣ ለግንባታና ለቤት ውስጥ እቃዎች መስሪያ፣ ለመድኃንትነትና ለአራዊቶች መጠለያ እንደሚያገለግሉ ገንዘቤ ያገኛሉ።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን እንስሳት የጀርባ አጥንት ያላቸውና የሌላቸው በማለት በሁለት ዋና ዋና ምድቦች በመደብ በተለያዩ ባህሪያቸው ላይ

በመመርኮዝ ደግም በአጥብዎች፤ አእዋፋት፤ ገበሎ አስተኔዎች፤ የእንቁራርት አስተኔዎች፤ አሣዎች ፣ ሶስት አፅቂዎችና በመሳሰሉት ምድቦች መመደብ እንድችሉ ማስተማር ነው፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች እንደ አፈር፣ እንሰሳት፣ ውኃ፣ ዕፅዋትና የመሳሰሉትን በማለት በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን አንዳንድ የተፈጥሮ ሀብቶችን መናገር እንድችሉ መምራት ነው፡፡

በዚህ ምዕራፍ ማጠቃለያ ላይ አከባብን ከብክለት እና ጥፋት ለመጠበቅ ለተፈጥሮ ሐብት እና ለአከባብ እንክብካቤ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን እንድያውቁ ማድረግ፡፡ በአከባቢ የሚጣሉት አንዳንድ ቁሶች አከባብን የሚበክሉ እና የሚያቆሽሹ ስለሆኑ መልሰው በመጠቀም ጉዳቱን መቀነስ እንደምቻል ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡

ይህ ምዕራፍ የተማሪን ግንዛቤ የሚያዳብር ተግባራት እና ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ስለዚህ መምህራን ሁሉንም ተማሪዎች በሚያሳትፍ መልኩ ተግባራት እና ጥያቄዎችን በማሰራት የተለያየ ዘዴ በመጠቀም መመዘን አለባቸው፡፡

የመማር ማስተማር ሂደትን ለማሳካት የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎች ብያንስ አነስተኛው የመማር ብቃት ደረጃ ላይ እንድደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## 3.1. የአየር ጠባይ እና የአየር ንብረት

ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠው የክፍሌ ጊዜ ብዛት-------------------9

**የዚህ ርዕስ ትምህርት ውጤቶች ፡**

**በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ ተማርው/ዋ**

- የአየር ጠባይ በየቀኑ የሚለዋወጥ የአየር ሁኔታ ነው በማለት ፊቺውን ይሰጣል/ትሰጣለች፣
- የአየር ጠባይን ምሳሌ ይሰጣል/ትሰጣልች፣
- የአየር ንብረት ማለት በአማካይ በአንድ አከባብ ለረጅም ግዜ የሚቆይ የአየር ጠባይ መሆኑን ይገልጻል/ትገልጻለች፣
- የአየር ንብረት ህይወት ባላቸው ነገሮች ላይ ያለውን ተፅእኖ ይግልጻል/ትገልጻለች፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

ይህ ርዕስ በአየር ንብረት እና በአየር ጠባይ መካከል ያለውን ልዩነት እና ምሳሌዎቻቸውን፣ የአየር ንብረት መለዋወጥ ምክንያቶች እና በአየር ንብረት መለዋወጥ ምክንያት ህይወት ባላቸው ነገሮች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ተፅዕኖችን በውስጡ የያዘ ነው፡፡

በአየር ንብረት መለዋወጥ ምክንያት የሚከሰቱ ተፅዕኖዎች ራብ፤ ድርቅ፤ የውሃ እጥረት፤ የዝናብ አጥረት እና ያለጊዜው የሚዘንብ ዝናብ፤ የጎርፍ አደጋ፤ የተለያዩ በሽታዎች፤ የአከባብ መበከል እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ለአየር ንብረት መለዋወጥ ምክንያት የሆኑት ደግሞ የደን መመንጠርና መቃጠል እንድሁም ከፋብሪካዎች የሚወጣ ጭስ ናቸው፡፡

የተማሪዎችን መማር ሂደት መራኪ ለማድረግ የዚህን ርዕስ ተምህርት ይዘቶች በአከባብው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በመያያዝ ማስተማር አስፈላጊ ነው፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

በዚህ ትምህርት ይዘት ውስጥ የተማሪዎችን የመማር ሁኔታን ከግብ ላማድረስ መምህሩ/ርቷ በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያሉትን የአየር ንብረት እና የአየር ጠባይ ስዕሎች እና ሌሎችን አጎልተው በማንሳት ማዘጋጀት አለበት/ባት፡፡

የአየር ንብረት ህይወት ባላቸው ነገሮች ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ለተማሪዎች ለማሳየት በአየር ንብረት ምክንያት የምመጡትን ችግሮች የሚያሳይ ስዕሎችን አዘጋጅ/ጂ፡፡ እንደዝሁም ይህንን ርዕስ ከአከባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናኘት በአየር ንብረት መለዋወጥ ምክንየት በአከባቢያቸው ላይ የደረሱ ጉዳቶች ካሉ ተማሪዎችን ለማስጎበኘት ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡ የወረዳቸውን የአየር ንብረት መረጃ እንዲያገኙ (ለምሳሌ የዝናብ ወቀት) ከወረዳቸው ባለሙያ ጋር እንድገናኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው፡፡

በአጠቃላይ የተማሪዎችን የመማር ዓላማ ለማሳካት የእለት እቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

### ሀ. የአየር ጠባይ

በአንደኛ ክፍል የአከባብ ሳይንስ ውስጥ የተማሩትን ፣ አራቱን የአንድ አመት ወቅቶች እና በእያንዳንዱ ወቅት ውስጥ የሚኖሩትን የአየር ሁኔታዎች ጋር የተያያዙትን አንዳንድ ጥያቂዎችን በመጠየቅ የዚህን ርዕስ ትምህረት መጀመር ነው፡፡

በወረዳቸው ውስጥ በአየር ጠባይ እና በወቅቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ከወረዳቸው የአየር ሁኔታ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ምሳሌዎች በመጥቀስ ተሳትፎአቸውን በማጠናከር ማስተማር ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በክረምት፣ በፀደይ፤ በበጋ እና በበልግ ወቅት በወረዳቸው ውስጥ የሚታዩትን የአየር ጠባዮች እንድለዩ እና የአየር ጠባይ በየሰዓቱ፤ በየቀኑ እና በየወቅቱ የሚቀያየር መሆኑን የአከባብያቸውን የአየር ጠባይ እንደ ምሳሌ በማንሳት ማስተማር ነው ፡፡ እንደዚሁም በስዕል የተደገፈ የአየር ጠባይ ኤሌሜንቶች በመዘርዘር እና በተለያዩ ምሳሌዎች ማስገንዘብ አሰፈላጊ ነው፡፡

ተማሪዎች በየግዜው የሚቀያየረውን የአከባብያቸውን የአየር ጠባይ በማነፃፀር በቡድን እንድወያዩ እና ውጤቱን ለክፍላቸው እንድያቀርቡ በማድረግ መማር ማስተማሩን ተጨባጭ ማድረግ ይቻላል፡፡

እንደ መግለፅ፣ የመስክ ጉብኝት፣ ጥያቄ እና መልስ፣ ውይይት እና የመሳሰሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎች በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡

## ለ. የአየር ንብረት

በወረዳቸው ውስጥ ለረጅም ጊዜ በተደጋጋም የሚታየው የአየር ሁኔታ ምንድን ነው? በማለት ሁሉንም ተማሪዎች በሚያሳትፍ መልኩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር ይቻላል፡፡ ይህ ጥያቄ ከተጠየቀ በኃላ ተማሪዎች በቡድን ወይም በግል በመሆን መልሳቸውን እንድመልሱ ማድረግ፡፡ በመጨረሻም የአየር ንብረት በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ በተደጋጋሚ ለረጅም ግዜ የሚታይ የአየር ጠባይ አማካይ ውጤት መሆኑን አከባቢያቸው ያለውን የአየር ንብረት ምሳሌ በመውሰድ ማስገንዘብ ነው፡፡

በዚህ ርዕስ የመማር ሂደት ውስጥ በአየር ጠባይ እና በአየር ንብረት መካከል ያለውን ትስስር እና ልዩነት ምን እንደ ሆነ ተማሪዎችን በማወያየት እና የተለያዩ ምሳሌዎችን እንድሰጡ በማድረግ ማስገንዘብ ነው፡፡

ተማሪዎች ዝናብ በወረዳቸው የሚዘንብበት ወራትን ለማወቅ እና የወረዳቸው የዝናብ ወራትን በግራፍ እንዲያገኙ መምህራን ከወረዳው የግብርና ባለሙያ ጋር እንደገናኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡ ተማሪዎች በወረዳቸው ዝናብ በብዛት የሚዘንብበት ወራትን የሚያሳይ ቀላል ግራፍ ላይ ውይይት በማድረግ ለክፍላቸው እንድያቀርቡ ማድረግና ግራፉን በመጠቀም ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ህይወት ባላቸው ነገሮች ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ የተለያዩ ምሳሌዎች እና የአየር ንብረት ለውጥ ያደረሳቸውን ጉደቶችን የሚያሳይ ስዕሎችን በመጠቀም ግንዛቤ መስጠት ነው። በመጨረሻም የአየር ንብረት ለውጥ በወረዳቸው ውስጥ የደረሰው ተፅዕኖ ካለ እንዲናገሩ እና የአየር ንብረት ተፅዕኖ ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ እንዲወያዩበት ዕድል መስጠት ነው።

የሰው ልጅ በአየር ሁኔታዎች መለዋወጥ ላይ ያለውን ድርሻ ተማሪዎች እንድወያዩበት እና ግንዛቤ እንድያገኙ ማድረግ ነው። ይህንንም፣ በአይር ንብረት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱትን የተለያዩ ተግባራትን ምሳሌ በመውሰድ እና በስዕል በማስደገፍ ማስተማር ነው።

በአየር ንብረት መለዋወጥ ምክንያት በወረዳቸው ውስጥ ህይወት ባላቸው ነገሮች ላይ የደርሰ ተፅዕኖ ካለ በግላቸው እንዲናገሩ ማድረግ።

በወረዳቸው ውስጥ የተመነጠረ እና የተቃጠለ የደን መሬት ካለ የደን መመንጠር እና መቃጠል ያደረሰውን ጉዳት እንዲናገሩ ጠይቃቸው/ቂያቸው።

## ተማሪዎች ሊያዳብሩት የሚችሉት የፈጠራ ችሎታ

በዚህ ርዕስ ሥር ተማሪዎች የመስክ ጉብኝት እንዲያደርጉ፤ በመረጃ ላይ በመመርኮዝ እና በማሰላሰል ትርጉም በመስጠትን የፈጠራ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።

## የምዘና ዘዴ

በዚህ ርዕስ ትምህርት ሂደትና መጨረሻ ላይ በተማሪ መፅሐፍ ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎችና ተግባራትን በግል እና በቡድን እንድሰሩ በማቀናጀት በተማሪዎች ላይ በየቀኑ የሚታየውን የባህር ለውጥ በመመዝገብ ድክመት ያለባቸውን ተማሪዎችን በመርዳት እና በማብረታታት ግብረ መልስ እየሰጡ መሄድ ነው።

ተግባራት እና ጥያቄዎችን እንደ ቤት ሥራ እና ክፍል ሥራ በመስጠት መመዘን ነው። ተማሪዎች የተግባር ስራቸውን በሪፖርት መልክ እንድያቀርቡ በማድረግ ብቃታቸውን እየመዘኑ መሄድ አስፈላጊ ነው።

በመጨረሻም ተማሪዎች በአየር ጠባይ እና በአየር ንብረት መካከል ያለውን ልዩነት መርዳታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። ብሚዘና ሰዓት ውጤታቸውን እየመዘገቡ መሄዱ ጥሩ ነው።

**የመልመጃ መልስ**

**የተግባር 3.1 መልስ ቤተማሪዎች መረጃ እና በሚያቀርቡት ሪፖርት ላይ ይወሰናል**

**የግንዛቤ ጥያቄ** - በተማሪዎች መፅሐፍ ውስጥ የተጠየቀው በአየር ንብረት መለዋወጥ ምክንያት የምመጡ ችግሮች ድርቅ፣ የምግብ አጥረት፣ የጎርፍ አደጋ፣ የተለያዩ በሽታዎች፣ የሶስት አፅቂዎች ወረራ እና ለሎችም ልሆኑ ይችላሉ። ለአየር ንብረት መቀያየር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የደን መቃጠል፤ የደን መመንጠር እና ከፋብሪካዎች የሚወጡ ጭሶች ይሆናሉ።

## 3.2. የወረዳችን ዕፅዋት

ለዚህ የትምህርት ርዕስ የተሰጠው የክፍሌ ጊዜ ብዛት-------------------9

**የዚህ ርዕስ ትምህርት ውጤቶች ፡**

**በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ ተማርው/ዋ**

- በወረዳቸው ውስጥ በብዛት የሚገኙትን ዕፅዋት ይለያል/ትለያለች፣
- ለዕፅዋት እድገት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ያሳያል/ታሳያለች፣
- ዕፅዋት ያላቸውን የተለያዩ ጥቅምችን ይለያል/ትለያለች።

### ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ርዕስ የመማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች በወረዳቸው ውስጥ በብዛት የሚገኙትን ዕፅዋት በመለየት በእድገታቸው እና በቁመታቸው መሰረት በተለያዩ ምድቦች ይመድባሉ።ዕፅዋት ህይወት ያላቸው ነገሮች ስለሆኑ ያድጋሉ። ለማደግ ደግሞ የፀሐይ ብርሃን፣ አፈር፣ አየር እና ውሃ ያስፈልጋቸዋል። የውሃ እና ፀሐይ ብርሃን ለዕፅዋት እድገት ማስፈለጋቸውን ተማሪዎች በተግባር መማር ይጠበቅባቸዋል።

እንዲሁም እፅዋት ለሰው ልጅ እና ለእንስሳት የላቸውን ጥቅም በጥቂቱ ማወቅ አለባቸው። ለምግብነት ስለ ሚውሉ የዕፅዋት አይነቶች ግንዛቤ እንድያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል።

## ቅድመ ዝግጅት

የእፅዋትን አካለ ክፍሎች ለማስተማር፣ የእፅዋትን ናሙና በጠርሙስ ወይም በተለያዩ ፕላስትኮች ውስጥ ማሳደግ፣ የዕፅዋትን ቁመት በየግዜው የሚለኩብትን ማስመሪያ እና ስዕል የሚያነሱበት ወፍራም ወረቀት አስቀድሞ ማዘጋጀት፡፡ ከእፅዋት የተመረቱ እቃዎች እና የእፅዋትን ምድብ የሚያሳዩ ስዕሎች ወይም ፖስተር፣ ለምግብ የሚውሉትን እፅዋት ስዕል ወይም ፎቶ የያዘ ካርድ፣ የእፅዋትን ጥቅም የሚያሳዩ ሌሎች የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን መዘጋጀት ያስፈልጋል ፡፡

የመስክ ጉብኝት እና የሚጎበኝ ቦታ አስቀድመው ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ የዚህን የትምህርት ይዘት ለማስጨበጥ ለእያንዳንዱ የትምህርት ክፍሌ ጊዜ እቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ በቡድን ውይይት፣ በእይታ፤ በመሰክ ጉብኝት፤ በተግባር እና በገለፃ ተማሪዎችን በማሳተፍ ማስተማር ነው፡፡ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በንቃት እንድሳተፉ መምህሩ/ርቷ የተለያዩ የዕፅዋት ናሙና፤ ስዕላቸውን እና ምድባቸውን የሚያሳይ ፖስተር መጠቀም አለበት/ባት፡፡

እፅዋት ለማደግ እና ለመኖር የፀሀይ ብርሃን ፤ አየር፤ ውሃ እና አፈር አስፈላጊ መሆኑን በተማሪዎች መፅሐፍ በተቀመጠው መሰረት በተግባር እንድ ደርሱበት ምቹ ሁኔታን መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡

የትምህርቱ ቀን ከመድረሱ በፊት ተማሪዎች ተግባር 3.3 እና 3.4ን በአንድ ግዜ እንድሰሩ አስቀድሞ እንድዘጋጁ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በሥራው ሂደት እና በተግባር ስራው አፈፃፀም ውስጥ በፀሐይ ብርሃን እና በውሃ ምክንያት በእፅዋት እድገት ላይ በየቀኑ የሚታዩ ለውጦችን እየመዘገቡ እንድሄዱ ማድረግ የመምህሩ/ርቷ ድርሻ ነው፡፡

በዚህ ተግባር ሥራ ውስጥ ተማሪዎች የምልከታ፤ የመስፈር፤ የመመደብ እና አጠቃላይ ሀሳብ መስጠት ክሎትን ያዳብራሉ፡፡

በእያንዳንዱ የተግባር ውጤት ላይ ተማሪዎች በግል ወይም በቡድን በመሆን እንድወያዩበት እና ቢያንስ ልደርሱቡት የሚገባ የመማር ብቃት ማግኘታቸውን መምህራን እያረጋገጡ መሄድ አስፈላጊ ነው፡፡

በወረዳቸው የሚገኙ የታወቁ የተለያዩ የእፅዋት ዓይነቶችን መለየት እንድችሉ ስማቸውን በመፃፍ ሪፖርት እንድያደርጉ በማድርግ በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን እፅዋት እንድያውቁ ማድረግ ነው። እነዚህን እፅዋት በዛፍ፤ በቀጥቋጦ፤ በሣራማ፤ በዛፍ ላይ ተጠምጥመው የሚያድጉ እፅዋት እና በመሬት ላይ በመተኛት የሚያድጉ እፅዋት እንድመድቡ በቡድን ስራ መልክ መስጠት።

በአከባብያቸው ለምግብነት፣ ለግንባታ፣ ለቤት ዕቃዎች መሥሪያ፣ ለመድኃንትነትና ለልብስ የሚውሉትን እፅዋት ለይተው እንዲዘርዝሩ መምራት ነው።

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ እፅዋትን በመነብኘት ስማቸውን ከዘረዘሩ በኃላ በተለያዩ የእፅዋት ምድቦች እንድ መድቡ በማድረግ ግንዛቤያቸውን እንድዳብሩ ማድረግ ነው።

በተጨማሪም የተለያዩ የእፅዋትን ስዕል ወይም ናሙና ወደ ክፍል በመምጣት እያዩ እንድማሩ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው።

በዚህ ርዕስ ውስጥ መምህራን በወረዳቸው የሚገኙትን የተለያዩ እፅዋትን ተጨማሪ ምሳሌ በመስጠት ትምህርቱን ተጨባጭ ማድረግ አለባቸው።

## ተማሪዎች ሊያደብሩ የሚችሉት የፈጠራ ችሎታ

ተማሪዎች በዚህ ትምህርት ውስጥ የተቀመጡትን የመማር ሂደት እና ተግባራትን በማከናወን ውስጥ ሳይንሳዊ የሆነውን መሰረታዊ ክህሎት የሆኑትን እንደ ምልከታ፣ ትንበያ፣ ሙከራ፣ ምደባ፣ የማጠቃልያ ሐሳብ መስጠት እና የሳይንዊ ሂደትን መለማመድን ያዳብራሉ።

በዚህ ርዕስ ውስጥ ተማሪዎች ለሳይንትስትነት መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ መሰረታዊ የሆኑ ሳይንሳዊ ክህሎቶችን ያዳብራሉ።

## የምዘና ዘዴዎች

በዚህ ርዕስ የትምህርት ሂደት መግቢያ ላይ ተማሪዎች በወረዳቸው ውስጥ ያሉትንና የምያውቁትን የእፅዋት ስሞች እንድዘረዝሩ በመጠየቅ እና እፅዋት ያላቸውን ባህሪይ በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር ይቻላል።

ተማሪዎች ለእፅዋት እድገት የፀሐይ ብርሃን እና ውሃ አስፈላጊ እንደሆነ እንድገነዘቡ ተግባር 3.3 እና 3.4ን እንድሰሩ በማድረግ ትክክለኛውን የሳይንሳዊ መንገድ ተከትለው እየሰሩ መሆናቸውን መከታተል ያስፈልጋል። በመጨረሻም የተግባር ሥራ ውጤታቸውን ሪፖርት

እንድያቀርቡ በማድረግ ግብረ መልስ መስጠት። ተማሪዎች በሪፖርታቸው ውስጥ በእፅዋት እድገት ውስጥ ያለውን ልዩነት እንድገልፁ በማድረግ ውሃ እና ፀሐይ ለእፅዋት እድገት አስፈላጊ መሆናቸውን የተገነዘቡ መሆነቸውን ማረጋገጥ ነው።

እያንዳንዱ ተማሪ በአከባቢው የሚገኙትን እፅዋት በእድገታቸው እና በባህሪያቸው መሠረት በተለያዩ ቡድን መመደብ መቻሉን/ለዋን በመመዘን በእነሱ ላይ የመጣውን የባህሪይ ለውጥ በመመዝገብ አበረታች የሆነ ግብረመልስ እየሰጡ መሄድ አስፈላጊ ነው።

ተማሪዎች በወረዳቸው ውስጥ ከሚገኙት እፅዋት መካከል ለምግብነት፤ ለመድኃንትነት፤ ለቤት ዕቃዎች መስሪያ፤ ለልብስ እና ለውበት የሚውሉትን እንድዘረዝሩ መጠየቅ።

በመጨረሻም እያንዳንዱ ተማሪ መድረስ በሚገባው የመማር ብቃት ላይ መድረሱን/ሱዋን ካረጋገጥክ/ሽ በኃላ ከመማር ብቃት ጋር የሚገናኙ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መመዘን እና ነጥብ መያዝ ይቻላል።

## የተግባር መልስ

**ተግባር 3.2**

ሥር፣ ግንድ፣ ቅጠል፣ ፍሬና አበባ (መልሱ በእፅዋቱ አይነት ላይ ይመረኮዛል)

**ተግባር 3.3 እና 3.4**

- እፅዋት ውሃ እና ፀሐይ ካላገኙ ማደግ አይችሉም

**ተግባር 3.5**

ተማሪዎች የትምህርት ቤት ግቢያቸውን እፅዋት እንድጎበኙ እና ሪፖርት እንድያቀርቡ ሁኔታዎችን በማመቻቸት በርፖርታቸው ላይ ግብረመልስ መስጠት።

**ተግር 3.6**

ተማሪዎች የቤት እቃ የሚሰሩባቸውን እፅዋት እንድዘረዝሩ እና እድወያዩበት በማድረግ ግብረመልስ መስጠት።

እንደዚሁም ተማሪዎች በተግባር 3.7 በአከባብያቸው ውስጥ ለመድኃንተነት የሚውሉ እፅዋትን የሚያውቁትን ሰዎች በመጠየቅ በክፍላቸው ውስጥ እንድወያዩበት በማድረግ ግብረ መልስ መስጠት

## 3.3. የወረዳችን እንስሳት

ለዚህ ትምህርት ይዘት የተሰጠው የክፍሌ ጊዜ ብዛት------------------15

**የዚህ ርዕስ ትምህርት ውጤቶች ፡**

**በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ ተማርው/ዋ**


- በአከባቢያቸው የሚገኙትን እንስሳት የጀርባ አጥንት ያላቸውና የሌላቸው በማለት በሁለት በመክፈል በውጫዊ አካል ክፍሎቻቸው ላይ በሚታዩት ሁናቴዎች እንስሳትን በአጥቢዎች፤ የገበሎ አስተኔዎች፣ አእዋፋት፣ አሣዎች፣ የእንቁራርት አስተኔዎች፣ ሶስት አፅቄወዎችና በሌሎች ምድቦች በመመደብ ስማቸውን ይናገራል/ትናገራለች፣
- ለእንስሳት መኖር የሚያስፈልጉትን ነገሮች ይዘረዝራል/ትዘረዝራለች።

## ዋና ዋና ነጥቦች

የዚህ ርዕስ ዋና ይዘት በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን እንስሳት የጀርባ አጥንት ያላቸውንና የሌላቸው ምድቦች በመመደብ በሁለቱ ምድቦች ሥር በአጥቢዎች፤ የገበሎ አስተኔዎች፤ አእዋፋት፤ አሣዎች፤ የእንቁራርት አስተኔዎች፣ ሶስት አፅቄወዎችና በመሳሰሉት ምድቦች መመደብ። እንደዝሁም በአከባብያችን ለሚገኙት እንስሳት መሰረታዊ የሆኑ አስፈላጊ ነገሮች እንደ ውሃ፤ ምግብ የመኖርያ ቦታ እና የመሳሰሉት መሆናቸውን ማስገንዘብ።

## ቅድመ ዝግጅት

- የተለያዩ እንስሳትን ስዕል ወይም ምስል የያዘ ካርድ በብዛት ማዘጋጀት
- ከዝህ በታች ባለው መሰረት የእንስሳትን ምደባ የያዘ ቻርት አስቀድሞ ማዘጋጀት



## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ በአንደኛ ክፍል የአከባብ ሳይንስ ውስጥ የተማሩትን የእንስሳት ምደባ ጋር በማያያዝ ማስተማር ያስፈልጋል። ይህ ማለት ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት የእንስሳትን ስዕል ወይም ምስል የያዙትን ካርድ ለቡድኑ በማከፋፈል ተማሪዎች እነዝህን እንስሳት በጸጉራቸው፣ በአካሄዳቸው፣ በእግራቸው ብዛት፣ በአረባባቸው፣ በምመገቡት ምግብ እና በመኖሪያቸው እድመድቡ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር።

በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን እንስሳት ስሞች በቡድን ወይም በግል አንድፅፉ በማድረግ በመፃፋቸው ውስጥ በተቀምጠው መሰረት እንስሳቱን የጀርባ አጥንት ባላቸውና በሌላቸው ምድቦች ከመደቡ ቦኃላ በአጥቢዎች፣ የገበሎ አስተኔዎች፣ አእዋፋት፣ አሣዎች፣ የእንቁራርት አስተኔዎች እና ሶስት አፅቄወዎች እድመድቡ ማድረግ።

በመጨረሻም ከዝህ በላይ የተቀመጠውን ቻርት በመጠቀም የእንስሳትን ምደባ ማጠቃለል አስፈላጊ ነው።


በተጨማሪም የወረዳቸው እንስሳት ዝርያቸውን ለማስቀጠል እና ለመኖር ምን እንደምያስፈልጋቸው ማስገንዘብ ያስፈልጋል። እነሱም ምግብ፣ ውሃ፣ መጠለያ እና የመኖሪያ ቦታ ናቸው። ስለዚህ ደን መመንጠር እና ደን ማቃጠል የመኖርያ ቦታ፤ ምግብ እና ውሃ እንድያጡ ስለምያደርግ ደንን ማንከባከብ አስፈላጊ መሆኑን ተማሪዎችን ማስገንዘብ ያስፈልጋል።


## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ

ተማሪዎች በመማር ሂደት እና የተሰጠውን ተግባር ስያከናውኑ ሳይንሳዊ መሰረት ያላቸውን እንደ ምልከታ እና ምደባን በመስራት ሳይንሳዊ ክህሎታቸውን ያዳብራሉ። ተማሪዎች በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን እንስሳት ለማወቅ እና ለማጥናት ተነሳሽንት ያገኛሉ።

## የምዘና ዘዴዎች

ተማሪዎች እንስሳትን የጀርባ አጥንት ባላቸውና በሌላቸው ምድቦች መድበው በአጥቢዎች፤ የገበሎ አስተኔዎች፤ አእዋፋት፤ አሣዎች፤ የእንቁራርት አስተኔዎች እና ሶስት አፅቄዎች መመደብ መቻላቸውን ለመለየት የእንስሳትን ስዕል ወይም ምስል የያዙትን ካርዶች ለተማሪዎቹ በመስጠት ተማሪዎቹ በግል ወይም በቡድን በመሆን በእንስሳት የምደባ ቻርት ላይ እድለጥፉ በማድረግ ግንዛቤያቸውን መመዘን።





ለምሳሌ: የእንስሳትን ስዕል ወይም ምስል የያዘ ካርድ

በመመዘን ሂደት ውስጥ ግንዛቤያቸውን በመለየት እና እያመዘገቡ በመሄድ በመጨረሻ ግብረ መልስ መስጠት።

በተጨማሪም ተማሪዎች በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን እንስሳት ስማቸውን በመዘርዘር ከዝህ በላይ በተቀመጠው መሰረት እንድመድቡ የቤት ሥራ መስጠት። የቤት ሥራቸውን ውጤት በማየት ግብረ መልስ መስጠት።

በመጨረሻም እያንዳንዱ ተማሪ መድረስ በሚገባው የመማር ብቃት ላይ መድረሱን/ዋን ካረጋገጥክ/ሽ በኃላ ከመማር ብቃት ጋር የሚገናኙ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መመዘን እና ነጥብ መያዝ ይቻላል።

**የተግባር 3.8 ጥያቄ መልስ**

በተማሪዎች መጽሓፍ ውስጥ በተጠቀው መሰረት ተማሪዎች በግል ወይም በቡድን ስማቸው የተዘረዘረውን እንስሳት በሁለት ክፍል በመክፈል የጀርባ አጥንት ባላቸውና በሌላቸው እንድመድቡ ማድረግ ነው።

## 3.4. የወረዳችን የተፈጥሮ ሀብቶች

ለዚህ ትምህርት ይዘት የተሰጠው የክፍሌ ጊዜ ብዛት-------------------9

**የዚህ ርዕስ ትምህርት ውጤቶች ፡**

**በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ ተማርው/ዋ**

- ለአከባቢ እና ለህብረተሰቡ የሚያገለግሉ በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶችን ይገልፃል/ትገልፃለች ።

**ዋና ዋና ነጥቦች**

በአከባቢያችን የሚገኙትን እንደ አፈር፣ ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ ውኃ፣ መዓድናትና የመሳሰሉትን ለይተው እንድናገሩና ለአከባቢው ማሃበረሰብ የሚሰጡትን ግልግሎት ማስገንዘብ ነው። ከዝህ በመነሳት ተማሪዎች በአከባብያቸው ለተለያዩ አገልግሎት መዋል የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን እንድዘረዝሩ ማድረግ ነው።

## ቅድመ ዝግጅት

መምህራን በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶችን ለይተው በማወቅ ስማቸው እና ያላቸውን ጥቅም አስቀድሞ በማሰብ ራሳቸውን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል። በወረዳቸው ውስጥ እንደ ተፈጥሮ ሀብት የሚወሰዱ ቁሶችን ስዕላቸውን ወይም ስማቸውን ከጥቅማቸው ጋር ከዝህ በታች በተዘጋጀው ሰንጠረዥ መሰረት አዘጋጅተው ተማሪዎች እንድገነዘቡ ማድረግ ከመምህራን የጠበቃል።

| ተ.ቁ | የተፈጥሮ ሀብት ስም | ያላቸው ጥቅም እና አገልግሎት |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |
| 6 | | |

ለዚህ ርዕስ ምቹ የሆነውን የመማር ማስተማር እቅድ በማቀድ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ነው።

## የመማር ማስተማር ዘዴ

በዚህ ርዕስ መግቢያ ላይ የወረዳቸው ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ምን ምን እደሆኑ ተማሪዎችን በመጠየቅ ግንዛቤያቸውን መለየት ነው ። በመቀጠል በተማሪው መፅሐፍ ላይ የተሰጠውን ምሳሌዎች ለተማሪዎች በማብራራት ሌሎች የተፈጥሮ ሀብት የሆኑትን ምሳሌዎች እና ጥቅማቸውን በቡድን በመሆን እድወያዩበት ወይም ሰዎችን በመጠየቅ ለክፍል እድያቀርቡ በመስጠት ተማሪዎች የትምህርቱን ይዘት እንድገነዘቡ ማድረግ።

ከተቻለ የተፈጥሮ ሀብት ስዕሎችን ተለቅ አድርጎ በማንሳት ለተማሪዎች ማሳየት አስፈላጊ ነው። በመጨረሻም በሰንጠረዡ በተቀመጠው መሰረት በአከባብያቸው የሚገኙ የትፈጥሮ ሀብቶች፤ አገልግሎታቸው እና ጥቅማቸውን በማዘጋጀት ለተማሪዎች በማቅረብ ማጠናቀቅ።

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን ለማዳበር

ተማሪዎች በአከባብያቸው ከሚገኙት ነገሮች መካከል የተፈጥሮ ሀብት የሆኑትና ያልሆኑትን በመለየት ለህብረተሰቡ ያላቸውን ጥቅም እና እንዴት ጥቅም ላይ መዋል እንደሚችሉ በማሰብ ስራ ላይ ማዋል የሚችል የፈጠራ ሃሳባቸውን መጠቆም ይቻላሉ።

## የምዘና ዘዴዎች

በዚህ ርዕስ መጀመሪያ ላይ በወረዳቸው ወይም በአከባቢያቸው የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች ስም እንድዘረዝሩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን መገምገም። በዚህ የመማር ሂደት ውስጥ ጥቂት የተፈጥሮ ሀብቶችን ምሳሌ በማሳየት ተጨማሪ ምሳሌ እንድሰጡ በማድረግ ያመጡትን የባህሪይ ለውጥ በመገምገም እየመዘኑ በመሄድ ወደ ትክክለኛው ፅንሰ ሃሳብ እንድ መጡ መምራት ነው።

**የተግባር 3.9 ጥያቄ መልስ**

በከባቢያቸው የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች ሰዎችን በመጠየቅ ለክፍል ሪፖርት እንድያቀርቡ እና በርፖርታቸው ላይ ግብረ መልስ በመስጠት እገዛ ማድረግ ነው።

## 3.5. የወረዳችን የአከባብ ጥበቃ

ለዚህ የትምህርት ይዘት የተሰጠ የክፍሌ ጊዜ ብዛት-------------------9

**የዚህ ርዕስ ትምህርት ውጤቶች ፡**

**በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ ተማርው/ዋ**

- መልሰው ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉትን ቁሶችን ይለያል/ትለያለች ፣

## ዋና ዋና ነጥቦች

እንድ ደን፣ አፈር፣ ውሃና አየር የመሳሰሉትን የተፈጥሮ ሃብቶችን ከጥፋትና ጉዳት ለመከላከል የሚከናወኑ ተግባራት የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ይባላል።

የዚህ ርዕስ ዋና ይዘቶች የአፈር ጥበቃ፣ የደን ጥበቃ፣ የውሃ እንክብካቤ፤ ቁሶችን መልሰው መጠቀም እና ቆሻሻን ወደ ኮምፖስት መቀየር፣ የተፈጥሮ እና የአከባብ ሀብትን ማንከባከብ

እና መጠበቅ የያዘ ነው፡፡ በዚህ ርዕስ ሥር ተማሪዎች የአከባቢያቸውን ሀብት እንዴት መንከባከብ እና መጠበቅ እንዳለባቸው መሰረታዊ ግንዛቤ ያገኛሉ፡፡ እንድሁም እንደ አፈር ፤ ውሃ እና ደን የመሳሰሉት የአከባቢያቸውን የተፈጥሮ ሀብት ላይ የደረሰውን ጉዳት በመጎብኘት በሚደረግላቸው እንክብካቤ ውስጥ ድርሻ እንድኖራቸው ማብረታታት ነው፡፡

በሌላ በኩል በአከባቢ የተጣሉትን ቆሻሻዎች እንደ ፕላስቲክ እና ተረፈ ምግቦች አከባቢን እንዳያቆሽሹ በምን መልክ መልሰን ስራ ላይ ማዋል እንደምቻል ግንዛቤ በማግኘት በትምህርት ቤታቸው እና መኖራቸው አከባቢ የአከባቢ ንጽህናን መጠበቅ ውስጥ ድርሻ እንዳላቸው ማስገንዘብ ነው፡፡ አሳታፊ የሆነ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም የዚህ ርዕስ ትምህርት ዓላማ ግቡን እንድመታ ማድረግ ከመምህራን ይጠበቃል፡፡

የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን በመጠቀም እና በተማሪው መፅሐፍ ውስጥ በተሰጠው ተግባር ተማሪዎችን መመዘን አስፈላጊ ነው፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

መምህራን ወደማስተማር ሂደት ከመግባታቸው በፊት የዚህን ትምህርት ይዘት ብቃት ማራጋገጥ የሚችል እቅድ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ የዚህ ርዕስ ዋና ዋና ይዘት ከህብረተሰቡ መኖሪያ አከባቢ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ተማሪዎች አከባቢያቸውን በመጎብኘት እንድማሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዝህ መምህሩ/ርተዋ የትምህርት ቤታቸውን አከባቢ ተማሪዎችን ለማስጎብኘት ቅርብ የሆነ ስፍራ በመምረጥ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅባታል፡፡

የተለያዩ የአከባቢ ጥበቃንና እንክብካቤንና ቆሻሻን መልሰው የመጠቀምን ዘዴ የሚያሳዩ ስዕሎች እና ምስሎችን በማዘጋጀት ትምህርቱን ተጨባጭ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በታች የተቀመጡትን ስዕሎችን እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል፡፡









**የመማር ማስተማር ዘዴ**

በዚህ ርዕሥ ይዘት ውስጥ የመማር ማስተማር ዘዴው በብዛት የሚያተኩረው ጉብኝት፣ የቡድን ስራ እና የምልከታ ዘዴዎች ናቸው፡፡

መምህራን ይህን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎች ከዚህን በፊት በአንደኛ ክፍል በአከባቢ ሳይንስ ውስጥ የተማሩትን ማነሳት ይቻላሉ፡፡ እነሱም የአከባቢ እና የግል ንፅህና መጠበቅ ጋር በማያያዝ ትምህርቱን መጀመር፡

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች የአከባቢያቸውን ተጨባጭ ሁኔታ እንደምሳሌ በመውሰድ እና በማስጎበኘት የተፈጥሮ አከባቢ እንደ አፈር እና ደን የሚደረገው እንክብካበ እንድሁም ጥበቃ እና እንክብካበ በማጣት ምክንያት በአፈር፤ ውሃ እና በደን ላይ የሚደርሱ ችግሮች ካሉ በማስጎብኘት ትምህርቱን ተጨባች ማድረግ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በተፈጥሮ ሀብት ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት ህይወት ባላቸው ነገሮች ላይ የደረሰ ጉዳት ካለ እንዲናገሩ ማብረታታት አስፈላጊ ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በትምህርት ቤታቸውና በአከባብያቸው በሚጣሉ አከባቢን የሚበክሉ ቆሻሻዎችን በማስጎብኘት እነዝህ ቆሻሻዎች የሚያስወግዱበት ዘዴ እና መልሰው ጥቅም ላይ የሚያውሉበት ዘዴ ላይ በቡድን ተወያይተው በትምህረት ቤት ግብ ውስጥ እንድለማመዱ

በማድረግ ማስተማር በጣም ጥሩ ነው፡፡ ለምሳሌ በፕላስቲክ እቃ ውስጥ ከዚህ በታች ባለው መልኩ የተለያዩ እፅዋት በመትከል አከባቢን ማሳዋብና እና ንፁህ ማድረግ ይቻላል፡፡



እንደዝህ አይነት ስራ ለተማሪዎች በፕሮጀክት መልክ በመስጠት በትምህርት ቤታቸው ግብ ውስጥ ሰርተው እንዲያሳዩ ማድረግ ይቻላል፡፡

ከምግብ የምተርፋት፤ ቅጠሎችን እና ለሎች ቆሻሻዎችን ቀብረው እንድበሰብሱ በማድረግ ወደ ማዳበርያነት ቀይረው ጥቅም ላይ እንድውል በማድረግ የአከባብን ንፅህና መጠበቅ እንደምቻል ተማሪዎችን ማስገንዘብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስለዚህም በአከባብያቸው እንደዝህ አይነት ተግባር ካለ እያስጎበኙ ማስተማር አስፈላጊ ነው፡፡

## የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታን ማዳበር

ከተጣሉ ቁሶች ለሌላ አገልሎት የሚውሉ እና አከባቢን ማስዋብ የሚችሉትን ስራዎች በመስራት የፈጠራ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ የተለያዩ ፕላስቲኮችን በመጠቀም የተለያዩ አከባቢን የሚያስውቡ አባበዎችን እና ለምግብነት የሚያገለግሉ ዕፅዋትን በመትከል መጠቀም ይቻላል፡፡

## የምዘና ዘዴዎች

በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የተሰጡትን ተግባራት በቡድን ወይም በግል እንድሰሩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን እየለዩ መሄድ፡፡ በለላ በኩል በመማር ማስተማር ሂደት ከአከባቢያችው ጋር በማገናኘት የአከባቢ ጥበቃ ምሳሌ እድሰጡ በማድረግ ሚዘና ማካሄድ ይቻላል፡፡
ተማሪዎች በአከባቢያቸው ጉብኝት ሂደት ውስጥ ማስታወሻ እየያዙ መሄድ እና ሪፖርት እንድያቀርቡ በማድረግ ችሎታቸውን እየመዘገቡ ድጋፍ መስጠት እና ግብረ መልስ መስጠት፡ ፡ በመጨረሻም ተማረዎች በአከባቢያቸው ጥበቃ ላይ ሪፖርት እንድያቀርቡ በማድረግ ብቃታቸው ምን ያህል እንደሆነ እየለዩ መሄድ ትምህርቱን ማጠቃለል፡፡

**የትግበራ መልሶች**

**ተግባር 3.10**

እርከን የተሰራብት መሬት አፈር በመያዝና በጎርፍ እንዳይሸረሸሩ በማድረግ በላዩ ላይ እፅዋት በቅለው ይታያሉ፡፡ እርከን የሌለው መሬት ደግሞ አፈሩ በጎርፍ እየታጠበ ባዶውን ይቀራል፤ እፅዋትም አይበቅሉበትም

**ተግባር 3.11** በአከባብያችን አከባብን ማቆሸሽ የሚችሉ ቁሶች የተለያዩ የውሃ ፕላስቲኮች፣ ፌስታሎች፤ የተሰባበሩ ጠርሙሶች፤ ከቤት የሚወጡ ቆሻሻዎች፤ ከምግብ ትራፊዎች እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## የምዕራፍ 3 መልመጃ መልሶች

**ሀ. እውነት ወይም ውሸት**

1. እውነት
2. እውነት
3. ውሸት
4. ውሸት
5. እውነት

**ለ. ምርጫ**

1. ለ
2. ለ
3. መ
4. መ
5. መ
6. ሀ
7. ሀ

**ሐ. አዛምድ**

1. ሀ
2. መ
3. ሠ
4. ለ
5. ሐ

**መ. አጭር መልስ**

1. የአየር ጠባይ ማለት በየእለቱ፣ በየቀናቱ፣ በየወራቱ እና በየወቅቱ የሚታይ የአየር ሁኔታ ማለት ነው፡፡የአየር ንብረት ማለት በአንድ አከባቢ በተደጋጋሚ ለረጅም ጊዜ ሳይቀያየር የሚታይ የአየር ሁኔታ ነው፡፡
2. የጎርፍ አደጋ፤ የዝናብ እጥሬት፤ ራብ፤ የተለያዩ በሽታዎች፡ የሶስት አፅቄዎች ወረራ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
3. ውሃ፡ የፀሐይ ብራን፤ አፈር እና አየር
4. እርከን መስራት፣ ቆሻሻን መልሰው ስራ ላይ ማዋል፣ እፅዋት መትከል፣ መንከባከብ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

# ምዕራፍ 4: ማህበራዊ አከባቢ

ለዚህ የትምህርት ይዘት የተመደበው የክፍሌ ጊዜ ብዛት---------------------- 45

**የምዕራፉ የመማር ውጠቶች፡**

**በዚህ ምዕራፍ ትምህርት ማጠቃላያ ላይ ተማሪዎች**

- የቤተሰብ አባላት እና የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ይገልፃሉ፣
- በቤተሰብ ጤና ተፅዕኖን ይገለፃሉ፣
- የትምህርት ቤት እና የትምህርት ቤት አከባቢ ማህበረሰብን አባላትን ይለያሉ፣
- ጓደኝነትንና በትምህርት ቤት ውስጥ ሊያከናውኑ የሚችሉ ተግባራትን ባህሪይ ያሳድጋሉ፣
- የትምህርት ቤት ህጎች እና ደንቦችን ያከብራሉ፣
- እጅ መታጠብንና ጥርስ መፋቅን ጨምሮ የግል እና አከባቢ ንፅህና መጠበቅ ዘዴዎችን ይገልጻሉ፣
- የራሳቸውን እና የትምህርት ቤታቸውን አከባቢ ንፅህና እንዴት መጠበቅ እንደሚቻል ይገልጻሉ፣

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ሦስት ዋና ዋና ርዕሶችን የያዘ ነው። የመጀመሪያው ርዕስ ለቤተሰብ አባላት እና የሚያስፈልጉ ነገሮችን በውስጡ ይይዛል። በዚህ ርዕስ ውስጥ ለቤተሰብ ኑሮ የሚያስፈልገትን ነገሮች እንደ ንፅህና፣ የአካል እንቅስቃሴ፣ ዕረፍት፣ በቂ እንቅልፍ ማግኘት እና የመሳሰሉት ናቸው። እንድሁም የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላትና የትምህርት ቤት አከባቢ መህረሰብን በውስጡ የያዘ ነው።

በሁለተኛ ርዕስ ውስጥ ደግሞ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ የጓደኝነት ግንኙነት በማሳደግ፣ በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ ሊኖራቸው የሚገቡ ባህሪያት በመረዳት ይለማመዳሉ።

የዚህ ምዕራፍ ሦስተኛ ርዕስ ደግሞ የሚያተኩረው በአከባቢ እና በትምህርት ቤት የንፅህና አጠባበቅ ላይ ነው።

### 4.1 የቤተሰብ አባላትና ለቤተሰብ የሚያስፈልጉ ተግባራት

ለዚህ የትምህርት ይዘት የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት-----------------------------19

**የዚህ ርዕስ የመማር ውጤቶች**

**በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ ተማሪው/ዋ**

- የቤተሰብ አባላትንና ለቤተሰብ ኑሮ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ይገልፃል/ትገልፃለች፣
- የቤተሰብ ጤና ተፅዕኖን ይገልፃል/ትገልፃለች፣
- የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላትንና የትምህርት አካባቢ መህበረሰብን ይለያል/ትለያለች፣

## ዋና ዋና ይዘቶች

በዚህ ርዕስ ሥር የቤተሰብ አባላትን እና የሚያስፈልጋቸው ነገሮችን፤ በቤተሰብ ጤና ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱ እንደ የግል ንፅህና መጠበቅ፤ የአካል እንቅስቃሴ ማድረግ፤ እረፍት ማድረግ እና በቂ እንቅልፍ መውሰድን ያጠቃልላል። የትምህርት ቤት ማህበረሰብ እና የትምህርት ቤት አከባቢ ማህበረሰብ መለየት ነው። ይህንን ርዕስ ለማስተማር የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም የተማሪዎችን እውቀት፣ሙያ እና አመለካከትን ሊያዳብሩ የሚችሉትን መጠቀም ያስፈልጋል።

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በመማሪያ መፅሓፍ ውስጥ ያሉትን መልመጃውችንና ተግባር ትክክለኛውን መልስ በመስጠት ለተማሪዎች ግብረ መልስ መስጠታ ያስፈልጋል።

**ቅድመ ዝግጅት**

ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚረዱ ተግባራትና ስዕሎች ከመማሪያ መፅሓፍ ላይ ከተቀመጡት ጋር በማዛመድ የተማሪዎችን ፍላጎት ማዕከል ባደረገ መልኩ ማዘገጀት ያስፈልጋል። ከዚህ ርዕስ ጋር የሚዛመዱ መርጃ መሳሪያዎች እና ተግባራትን ቀድሞ በማዘጋጀት የመማር መስተማሪን ምቹ ማድረግ ያስፈልጋል። የግል ንፅህና ጥቅም፣ የአካል እንቅስቃሴ እና በቂ ዕረፍት መውሰድ የሚሉትን ርዕሶችን ለማስተማር በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

መምህሩ/ርቷ የዚህን ርዕስ ትምህርት ከመጀመሩ/ዋ በፊት ተማሪዎችን ለማበረታታት እና ለማነቃቃት የተለያዩ የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለበት/ባት። ለምሳሌ የቤተሰብ አባላት እነማን እንደሆኑ እና የሥራ ድርሻቸው ምን እንደሆነ መጠየቅ እና ሁሉም ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲናገሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

የተማሪዎችን የመማር ብቃታቸውን ለመገምገም የግል፣ የቡድን፣ እና ክፍል ውስጥ በሚያደርጉ ተሳትፎ ለምሳሌ

- ለቤተሰብ የሚያስፈልጉ ተግባራት እና ጥቅማቸውን

- የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላት እነማን እንደሆኑ
- የትምህርት ቤት አከባቢ ማህበረሰብ እነማን መሆን እንደሚችሉ

በዚህ ርዕስ ሥር ተማሪዎች የተለያዩ እውቀትን፣ ግንዛቤ እና ሙያን የሚያዳብሩበት ስለሆነ በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የሚገኙ ስዕሎችን በደንብ በመረዳት ከግል ህይወታቸው ጋር እንዲያያይዙ ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም በግል፣ በቡድን እና ክፍል ውስጥ በሚያደርጉት ተሳትፎ የተማሪዎችን ደረጃ መለየት ይቻላል። የተማሪዎችን የመማር ብቃታቸውን ለማሻሻል ትምህርቱን ከግል ህይወታቸው ተሞክሮ ጋር እንዲያያዝ ማድረግ ያስፈልጋል። የተለያዩ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ለተማሪዎች የቤት ሥራን እንድሰሩና ትምህርቱን ከግል ህይወታቸው ጋር እንዲያያይዙ በማድረግ ትምህርቱን ተጨባጭ ማድረግ ይቻላል።

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ ማገዝ

የዚህ ርዕስ የመማር ማስተማር ሂደት ስር ተማሪዎች ፈጠራ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

### የምዘና ዘዴዎች

ተማሪዎች በግል፣ በቡድን እና ክፍል ውስጥ በሚያደርጉት ተሳትፎ ውስጥ ተከታታይ የሆነ ሚዘና ማካሄድ ይቻላል። ለትምህርቱ ዓላማ ግብ መምታት የእያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎ መመዝገብ ያስፈልጋል። በዚህ ርዕስ ስር ተማሪዎች ችሎታ፣ ግንዛቤ እና ክህሎትን እያዳበሩ መሆናቸውን በመከታተል ገንቢ ሀሳብ መስጠት ያሰፈልጋል። በዚህ ርዕስ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎችን ጥያቄ በመጠየቅ እና በማወያየት መገምገም ያስፈልጋል። መምህራን ተማሪዎች በሪፖርት መልክ ለክፍል የሚያቀርቡትን በመከታተል ውጤታቸውን እና ግንዛቤያቸውን በመለየት እገዛ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 4.2 የትምህርት ቤት ማህበረሰብ በጋራ ሊያከናውኑ የሚችሉት ተግባራት

ለዚህ የትምህርት ይዘት የተሰጠው የክፍለ ግዜ ብዛት ------------------------ 19

**የዚህ ርዕስ ትምህርት ውጤቶች**

**በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ ተማሪው/ዋ**

- ጓደኝነትንና በትምህርት ቤት ውስጥ በጋራ ልያከናውኑ የሚችሉትን ተግባራትን በማጎልበት በተግባር ያሳያል/ታሳያለች፣
- የትምህርት ቤት ደንብ እና ሥርዓትን ያከብራል/ታከብራለች።

## ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ርዕስ ውስጥ ተማሪዎች አብረው የመጫወት እና በአቅማቸው የሚችሉ ሥራዎችን የመስራት የሚያዳብሩበት ዕውቀትን የሚያገኙበት ነው። የተማሪዎችን እውቀት፣ የሥራ ክህሎት እና አመለካከት ለማዳብር ይሚያግዙ የተለያዩ የመማርና የምዘና የሚቀርቡበት ነው። በዚህ ርዕስ የመማር ሂደት ውስጥ በመማሪያ መፅሓፍ ውስጥ የተሰጡትን ጥያቄዎችን በትክክል መስራታቸውን ማረጋገጥ እና ግብረ መልስ መስጠት ያስፈልጋል።

### ቅድመ ዝግጅት

በቤተሰባቸው ውስጥ ያዳበሩትን ልምድ በክፍል ተማሪዎች ጋር እንዲለዋወጡ በማድረግ ችሎታቸውን እንዲያደብሩ ለማድረግ ዝግጅት ማድርግ ያስፈልጋል። ተማሪዎች ከክፍል ውጪ እንደየችሎታቸው በሚችሉት ነገር ላይ ሚና እንድጫወቱ ለማበረታታት ዕቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ተማሪዎች በቤተሰብ ውስጥ ያላቸውን ልምድ መሰረት በማድረግ የትምህርት ቤት ደንብና ሥርዓት አከባበር ላይ በትምህርት ቤት ውስጥ ሚና እንድጫወቱ ማበረታታት ነው።

አብረው የመጫወት፣ የመስራት እና የትምህርት ቤት ሥርዓትና ደንብ ማክበር ላይ የተማሪዎችን ችሎታ ለማሻሻል የተለያዩ መዝሙሮችን ማዘጋጀት። በትምህርት ቤት እና ትምህርት ቤት አከባቢ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለመመልከት ዕቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ለትምህርት ቤት ማህበረሰብ እና በትምህርት ቤት አከባቢ ለሚገኙ ህብረተሰብ የሚያስፈልጉ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ እንዲያውቁ ማድረግ።

### የመማር ማስተማር ዘዴ

የመማር ማስተማር ሂደት የክፍል ውስጥ ትምህርትን ከአከባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በመያያዝ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲያቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል። ተማሪዎችን ከክፍል ውጪ በቡድን በማደራጀት የተለያዩ ጫዋታዎችን እንዲጫወቱ በማድረግ የጫወታ ህግ እና ደንብን ማክበርን ማለማመድ ያስፈልጋል። እንዲሁም የተለያዩ መዝሙሮችን በማዘመር ትምህርቱን ይበልጥ ተማሪዎችን የሚስብ ማድረግ ።

ተማሪዎች አብሮ መጫወት እና የአኗኗር ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ ማድረግ፤ የሥራ እና የጫወታ ደንብ እና ሥርዓቶችን እንዲለማመዱ ማድረግ ያስፈልጋል። በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያለውን ሥዕል እና የተግባር ስራ መሰረት ቅደም ተከተላቸውን በመከተል በክፍል

ውስጥ እና ከክፍል ውጪ በግል እና በቡድን ተግባር ላይ ማዋል፡፡ በተጨማሪም የቤት ሥራ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ማህበረሰቡ በጋራ የመኖር እሴት ውስጥ የተለያዩ ለማህበራዊ አገልግሎት የሚውሉ ነገሮች እንዴት የማህበረሰቡን ፍላጎት እንደሚያሟሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ ማድረግ

በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ የፈጠራ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## የምዘና ዘዴዎች

ተማሪዎች ከዚህ በፊት ባላቸው እውቀት እና ከተማሩት ትምህርት ጋር በማያያዝ ሚዘና ማካሄድ ነው፡፡ በትምህርቱ አቀራረብ ላይ በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያለውን ተግባር እና ሥዕል ለትምህርቱ ዓላማ ግብ መምታት በሚያስችል መልኩ በግልና በቡድን እንድሰሩ ክፍል ውስጥ መጠየቅ፡፡ ተማሪዎች በማወያየት እና በማሠራት የሚያቀርቡትን በመከታተል የእያንዳንዳቸው  ተሳትፎ በተከታታይ በመመዝገብ ሚዘና ማካሄድ ይቻላል፡፡

### 4.3 የግልና እና የትምህርት ቤት ንፅህናን መጠበቅ

ለዚህ የትምህርት ይዘት የተሠጠ የክፍለ ግዜ ብዛት-------------------7

**የዚህ ርዕስ ትምህርት ውጤቶች**

**በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጠቃላያ ላይ ተማሪው/ዋ**

- የግል እና የትምህርት ቤት ንፅህና ጥቅምን ይገልፃል/ትገልፃለች፣
- የግል እና የትምህርት ቤት ንፅህና አጠባበቅ ዘዴን ይገልፃል/ትገልፃለች፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ርዕስ ስር ተማሪዎች የግል ንፅህና ምንነት እና ለሰው ልጅ ያለው ጠቀሜታ፤ የግል እና የትምህርት ቤታቸውን ንፅህና አጠባበቅን ይማራሉ፡፡ ርዕሱን የማስተማር ሂደት ውስጥ በተማሪዎች መፅሀፍ ውስጥ የተሰጠውን መልመጃ እና የተግባር ጥያቄዎችን ማሰራት፡፡ የተማሪዎች ተሳትፎ ማሳደግ እና ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

# ቅድመ ዝግጅት

በተማሪዎች መፅሀፍ ውስጥ የተሰጡትን ተግባርራት መሰረት በማድረግ ተማሪዎች ስለ ግል እና ትምህርት ቤት ንፅህና ያላቸውን ልምድ እርስ በራሳቸው እንዲማማሩ ለማድረግ የሚያስችል ዕቅድ ማዘጋጀት፡፡

በትምህርት ቤት እና በግል ንፅህና ውስጥ ህግ እና ደንብን በማክበር ተማሪዎች ሚና እንድጫወቱ ለማድረግ የሚያስችል ዕቅድ ማዘጋጀት፡፡ ተማሪዎች በግል እና በቡድን በመሆን የትምህርት ቤታቸውን ግቢ ንፅህና አንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው የሚያስችላቸውን እውቀት እንዲያገኙ ማድረግ፡፡ ትምህርቱን ዓላማ የሚሳካ ዕቅድ ማዘጋጀት፡፡ ጎደኛሞች ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ እንዴት ንፅህናቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው ግንዛቤ ይሚሰጥ እቅድ ማዘጋጀት፡፡

# የመማር ማስተማር ዘዴ

የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የክፍል ውስጥ ትምህርትን ከአከባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማያያዝ ተማሪዎች የግል እና የትምህርት ቤት ንፅህና አጠባበቅ ላይ ሐሳብ እንድያቀርቡ ማድረግ፡፡ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ በቡድን በማደራጀት የተለያዩ የግል እና የትምህርት ንፅህና ላይ እንድሳተፉ ማድረግ እና አብሮ የመስራት ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ በማድረግ የሥራ ተነሳሽነትን እንዲያዳብሩ ማድረግ ያስፈላጋል፡፡

# የምዘና ዘዴዎች

በዚህ ተመህርት መግቢያ ላይ ተማሪዎች ከዚህ በፊት ስለንፅህና አጠባበቅ ያላቸውን እውቀት መሰረት በማድረግ ለክፍል ተማሪዎች እንዲናገሩ በማድረግ በጥያቄና መልስ መመዘን ያስፈልጋል፡፡ በትምህርቱ አቀራረብ ላይ በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያለውን የተግባር ስራ እና ሥዕል ለትምህርቱ ዓላማ ግብ መምታት በሚያስችል መልኩ በግል፣ በቡድን እና ክፍል ውስጥ በሚያደርጉት ተሳትፎ በተከታታይ ሚዘና መገምገም፡፡ በዚህ ርዕስ ላይ ለትምህርቱ ዓላማ ግብ መምታት ተማሪዎች በጋራ የመስራት ባህል ማዳበራቸውን መጠየቅ፣ በማወያየት እና በመስራት ተማሪዎች የሚያቀርቡትን በመከታተል የእያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎ መመዝገብ ያስፈልጋል፡;

# የምዕራፍ 4 የመልመጃ መልሶች

**እውነት/ውሸት**

1. እውነት 2. ሀሰት 3. እውነት

**የምርጫ ጥያቄዎች መልሶች**

1. ሐ 2. መ 3. ሐ 4. ሐ 5. ለ 6. መ

**የአጫጭር መልስ ጥያቄዎች**

1. የሰውነት እንቅስቃሴ፣ የቤትና የቤተሰብ ንፅህ፣ የምግብ ንጽህና፣ እረፍትና በቂ እንቅልፍ
2. ገላን መታጠብ፣የጥርስ ንጽህና፣ የልብስ ንጽህና፣ እግር መታጠብ፣ ፊት መታጠብና የመሳሰሉት
3. ጤናማ ለመሆን፤ በሽታን የሚያመጡ ነፍሳትን ለማስወገድ፤የግል ሥራን ለማከናወን እና ለውበት።

# ምዕራፍ 5: ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ---------------------------25

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጠቶች፡**

**በዚህ ምዕራፍ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ ተማሪዎች**

- የትራፍክ ደንቦችን በመግለፅ ሥራ ላይ ያውላሉ
- በደም ንኪኪ የሚተላለፉ እንደ ኤች. አይ. ቪ. ያሉ በሽታዎችን ለመከላከል የሚረዱ ባህሪያትን ያዳብራሉ፡፡

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ትኩረት የሚሹ ሁለት ጉዳዮችን በውስጡ የካተተ ነው፡፡ እነሱም፣ በመኪና መንገድ ላይ ልደረግ የሚገባ ጥንቃቄ እና በደም ንኪኪ ሊተላለፉ ከሚችሉ በሽታዎችን እራስን መጠበቅን ናቸው፡፡ በዚህ ርዕስ ሥር የተማሪዎች የመማር ብቃት ጋር ይሄዳል ተብለው የታሰበው የትራፍክ ደንቦችን መረዳት እና ሥራ ላይ ማዋል፤ እንደ ኤች.አይ.ብ/ ኤድስ ያሉ በደም ኒኪኪ ከሚተላለፉ በሽታዎች ሕፃናት እራሳቸውን እንድጠብቁ አመላካከታቸውን መቀየር ነው፡፡

## 1.1. በመኪና መንገድ ላይ የሚደረግ ጥንቃቄ

ለዚህ የትምህርት ይዘት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት -----------------12

**የዚህ ርዕስ ትምህርት ውጤቶች**

**በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጠቃላያ ላይ ተማሪው/ዋ**

- የትራፍክ ደንቦችን በመግለፅ ሥራ ላይ ያውላል/ታውላለች፡፡

## ዋና ዋና ነጥብ

ይህ ርዕስ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ከሆኑት ውስጥ እንደ የትራፍክ ደንቦችና በመኪና መንገድ ላይ ሊደረጉ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች ላይ ያቶኩራል፡፡ በዚህ ደረጃ ላይ የተማረዎች የመማር ችሎታ ጋር በሚመጥን ሁኔታ የትራፍክ ደንቦችን መረዳት እና ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ነው፡፡

# ቅድመ ዝግጅት

በተማሪዎች መፅሀፍ ውስጥ የተሰጠውን ተግባር መሰረት በማድረግ የትራፍክ ደንብ የሚያሳይ ሠንጠረዥ በቅድሚያ ማዘጋጀት ያስፍልጋል፡፡ በተጨማሪም የትራፍክ ፖሊስን ቀድሞ በማወያየት ትምህርቱን ለመስጠት እንዲዘጋጁ ማድረግ ነው፡፡

# የመማር ማስተማር ዘዴ

ተማሪዎች በአከባቢያቸው አይተው የሚያውቁትን የትራፍክ አደጋ ካለ እንዲናገሩ እድል መስጠት፣ የትራፍክ አደጋን ለመቀነስ የሚረዱ ደንቦች ላይ እንዲወያዩ ማበረታታት፡፡ የእያንዳንዱን ደንቦች እንዴት ወደ ተግባር መቀየር እንደሚችሉ እንድገልፁ መጠየቅ እና ተሣትፎአቸውን ማድነቅ የስፈልጋል፡፡

ልጆች ራሳቸውን እንደት ከመኪና አደጋ ሊከላከሉ እንደሚችሉ ትምህርት ቤቱ ከተማሪዎች ቤተሰብ ጋር ውይይት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እንድሁም የሰንደቅ-ዓላማ አከባበር ላይ ለተማሪዎች በትራፍክ ደንብ ላይ እና ራሳቸውን እንደት ከትራፍክ አደጋ መጠበቅ እንዳለባቸው በየግዜው ትምህርት እና ግንዛቤ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

# ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ ማድረግ

ተማሪዎች የመንገድ ዳር የትራፍክ መብራት እንድሰሩ ማበረታታት

# የምዘና ዘዴዎች

የተማሪዎችን ውይይት መከታተል እና አፈፃፀማቸውን መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ጥያቄ በመጠየቅ፣ቴስት በመስጠት መመዘንና ግንቢ ግብረ መልስ መስጠት በግዜው መደረግ የሚገባ ተግባር ነው፡፡

**የተግባር 5.1 ጥያቄ መልስ**

1. በመኪና መንግድ ላይ መጫወት፣ ግራና ቀኝ ሳያዩ የመኪና መንገድን ማቋዋረት፣ ለእግረኛ ከተፈቀደው መንገድ ውጪ መሄድና የመሳሰሉት
2. የግራ አቅጣጫን መንገድ በመያዝ መጓዝ፣ በዜብራ ምልክት ላይ ብቻ መንገድን መቋረጥ፣ የትራፊክ ማብራት ምልክትን ማክበር

# 1.2. የራስን ጤንነት መጠበቅ

ለዚህ የትምህርት ይዘት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት -----------------13

**የዚህ ርዕስ ትምህርት ውጤቶች**

**በዚህ ርዕስ ትምህርት ማጠቃላያ ላይ ተማሪው/ዋ**

- በደም ንኪኪ የሚተላለፉ እንደ ኤች. አይ. ቪ. ያሉ በሽታዎችን ለመከላከል የሚረዱ ባህሪያትን ይናገራል/ትናገራለች፣
- ስለት ያላቸውን ዕቃዎች ከሌላ ሰው ጋር በጋራ ከመጠቀም ይቆጠባል/ትቆጠባለች ::

## ዋና ዋና ነጥቦች

በደም ንኪኪ ከሚተላለፉ በሽታዎች ራስን ለመጠበቅ ስለታማ ዕቃዎችን በጋራ ከመጠቀምና የሰውን ደም ከመነካካት መቆጠብ አስፈላጊ መሆኑን ማሪዎችን በደንብ ማስተማር ነው። በመጨርሻም በደም ንኪኪ ምክንያት ሊከስቱ የሚችሉ አደጋዎችን በመረዳት የባህሪይ ለውጥ እንድያዳብሩ ይጠበቃል።

## ቅድመ ዝግጅት

የተለያዩ ፅሁፎች፣ ቻርቶች፣ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ና በሌሎች በደም ንኪኪ የሚተላለፉ ሽታዎች ላይ ትምህርት ሰጪ የሆኑ የተለያዩ ፖስተሮችን በቅድምያ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ከተቻለ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ ትምህርት መስጠት የሚችል የጤና ባለሙያን መጋበዝ ያስፈልጋል።

## የመማር መስተማሪ ዘዴ

በቅድምያ ተማሪዎችን ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማድረግ። በመቀጠል ተማሪዎችን በቡድን እያደራጁ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ እንዲወያዩ ማድረግ። በዚህ ውይይት ላይ በኤች አይ ቪ/ኤድስ በህፃናት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ላይ እንዲወያዩ ማበረታታት ያስፈልጋል።

ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚተላላፍባቸው መንገዶችን ተማሪዎች በትክክል እንድያውቁ ማድረግ ያስፈልጋል። ሕጻናት ስለታማ ዕቃዎችን ብጋራ እንዳይጠቀሙ መምከር ያስፈልጋል።

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ ማድረግ

የተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ የሚረዳቸው የመማር ማስተማር ዘዴን በመጠቀም ኤች አይ ቪ/ኤድስ የማይተላለፍባቸው መንገዶች ላይ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች በጭውውት መልክ እንድያቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## የምዘና ዘዴዎች

ተማሪዎች የሚያደርጉትን ውይይት ማየት እና ውጤታቸውን መመዝገብ የስፈልጋል፡፡ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የሰጡትን መልስ መቀበል፤ በድራማ መልክ ክፍል ውስጥ ሲያቀርቡም በደንብ መከታተል እና መጨረሻ ላይ ግብረ መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

### የተግባር 5.2 መልስ

የተማሪዎችን ዘገባ ከአደመጥክ/ሽ በኃላ ተጨማሪ መረጃዎችን መስጠት ትችላለህ/ያለሽ፡፡ እነሱም፣ የግል ንፅህና መጠበቅ፣ ከደም ንኪኪ ራስን መጠበቅ፣ ክትባት መውሰድ፣ ስለታማ ዕቃዎችን በጋራ ያለመጠቀም

**የምዕራፍ 5 የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ**

**ሀ. እውነት/ሀሰት**

1. እውነት 2. እውነት 3. ሀሰት

**ለ. የምርጫ ጥያቄዎች መልስ**

**1. ለ 2. ለ 3.ሀ**

**ሐ. የትክክለኛውን መልስ ስጥ**

1. በመኪና መንገድ ላይ ግራውን ይዞ በመጌዝ በዘብራ ለይ ብቻ መንገድን ማቋረጥ
2. የተግባር 5.1 ን ተመልከት/ቺ

# የአካባቢ ሳይንስ መርሃ ትምህርት

# ሁለተኛ ክፍል

| 2ኛ ክፍል: ምዕራፍ 1 | 2ኛ ክፍል: ምዕራፍ 1 የሰውነት አካል ክፍሎች (ክፍለ ጊዜ 45) | የመመር ዘዴዎች | ተከታታይ ምዘና |
| --- | --- | --- | --- |
| • ውጫዊ የአካል ክፍሎችን ይለያሉ::<br>• የተለያዩ ውጫዊ የአካል ክፍሎችን ተግባራት ይለያሉ::<br>• የስሜት አባለ አካላትን ተግባራት ይዘረዝራሉ::<br>• ልዩ ቁሶችን ባህሪያቸውን መሰረት በማድረግ በስሜት አባለ አካላታቸው ይለያሉ::<br>• የብርሃን ምንጮችን ይዘረዝራሉ:: | 1.1 ውጫዊ የአካል ክፍሎቻችንና የስሜት አባለ አካላት **(ክፍለ ጊዜ 15)**<br>• አይን፣ጆሮ፣ ምላስ፣ አፍንጫ እና ቆዳ<br>• የውጫዊ የአካል ክፍሎች ተግባራት (ራስ፣ እግር፣ጸጉር እና ወዘተ)<br>• የስሜት አባለ አካላት ተግባራት<br>1.2 ልዩ ቁሶችን ባህሪያቸውን መሰረት በማድረግ በስሜት አባለ አካላት መለየት (ቀለም፣ ጥንካሬ፣ ልስላሴ፣ መጠን፣ ቅርጽ፣ ወዘተ) **(ክፍለ ጊዜ 15)**<br><br>1.3 የብርሃን ምንጮች **(ክፍለ ጊዜ 15)** | ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት:<br>• የሰውን ውጫዊ አካል ክፍሎችን በስዕል፣ በሞዴል ወዘተ እንዲስሉ እና እንዲያሳዩ ማድረግ እና ተግባሮቻቸውን እንዲገልጹ ማበረታታት::<br>ሰውነታችን የተገነበው:<br>• ከራስ፣ ከትከሻ፣ ከክርን፣ ከእግር፣ ከጉልበት …<br>የስሜት አባለ አካላትን:<br>• አይን፣ ምላስ፣ አፍንጫ፣ ጆሮ ፣ ቆዳ<br>• የተለያዩ የብርሃን ምንጮችን የተፈጥሮ ወይንም ሰው ሰራሽ በማለት እንዲለዩ ማድረግ::. | 2 ተማሪዎች በተለያዩ ውጫዊ የአካል ክፍሎች ተግባራት ላይ በሚወያዩበት ጊዜ ክህሎት፣ ዕውቀት እና ፍላጎታቸውን መመዘን<br>• የምልከታ ውጤትን መመዝገብ<br>• በታየው ክፍተት ላይ ገንቢ የሆነ ግብረ-መልስ መስጠት<br>• የመማር ማስተማር ዘዴኣቸውን እንዲያሻሽሉ የሚረዳቸው ገንቢ እና |

| 2ኛ ክፍል: ምዕራፍ 2 | 2ኛ ክፍል: ምዕራፍ 2 የወረዳችን መገኛ (ክፍለ ጊዜ 34) | የመማሪያ ዘዴዎች | ተከታታይ ምዘና |
| --- | --- | --- | --- |
| ▪ የመገኛን ምንነት ይገልጻሉ። <br> ▪ የመገኛን ምንነት ግልጽ ያደረጋሉ። <br> ▪ የወረዳቸውን መገኛ ያሳያሉ። <br> ▪ የወረዳቸውን መገኛ ከአጎራባች ወረዳዎች ጋር በማነጻጸር ያሳያሉ። <br> ▪ ቀላል ካርታ በማንሳት ታዋቂ ቦታዎችን ያሳያሉ። <br> ▪ ወረዳቸውን የሚያዋስኑ ወረዳዎችን ስም ይጠራሉ። | 2. መገኛ <br> 2.1. የወረዳችን መገኛ <br> (34 ክፍለ ጊዜ) <br> ▪ የመገኛ ምንነት <br> ▪ የአንጻራዊ መገኛ ምንነት <br> ▪ የወረዳችን የአንጻራዊ መገኛ <br> ▪ የወረዳችን ታዋቂ ቦታዎች መገኛ <br> ▪ የጎረቤት ወረዳዎች ስምና መገኛ | ▪ ተማሪዎች ስለአንጻራዊ መገኛ የሚያዉቁትን እንዲናገሩ መጠየቅ። <br> ▪ ተማሪዎች የወረዳቸውን አንጻራዊ መገኛ እንድገልጹ መጠየቅ። <br> ▪ ተማሪዎች የመኖሪያ ቤታቸውን፣ የትምህርት ቤታቸውንና የወረዳቸውን በንድፍ ካርታ ላይ እንዲያሳዩ ማድረግ። <br> ▪ ተማሪዎች ቀላል ካርታ መንደፍ ወይም ማንሳት መቻል አለባቸው። <br> ▪ ተማሪዎች የወረዳቸውን ካርታ እንዲያነሱ ማድረግ። <br> ▪ ተማሪዎች የአጎራባች ወረዳዎችን መገኛ ከንድፍ ካርታ ላይ በመመልከት እንዲገልጹ ማድረግ። | • ተማሪዎች ለጥያቄዎች የሚሰጡትን መልስ መከታታል <br> • ተማሪዎች በወረዳቸው ያሉትን ጠቃሚ ሥፍራዎች የማሳየት ልምምዳቸውን መሻሻል መከታታል <br> • ተማሪዎች ቀላል ካርታ መንደፍ ወይም ማንሳት ላይ ያላቸው ተሳትፎ መመልከት <br> • ቀጣይነት ያለው ክትትል መስጠት፤ ምሳሌ፣ ቀላል ካርታ <br> • ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠትና መመዝገብ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ▪ ተማሪዎች ኮምፓስ አቅጣጫን ለመለየት የሚረዳ መሣሪያ መሆኑን እንዲገልጹ ማድረግ<br>▪ ተማሪዎች በወረዳቸው ያሉትን ጠቃሚ ሥፍራዎች እንዲያጠኑ የቤት ሥራ መስጠት | • የተማሪዎችን ዘገባ በመመልከት ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት<br>• ተከታታይ ምዘና ማካሄድ |

| 2ኛ ክፍል: ምዕራፍ 3 | 2ኛ ክፍል: ምዕራፍ 3 የተፈጥሮ አካባቢ (ክፍለ ጊዜ 45) | የመመር ዘዴዎች | ተከታታይ ምዘና |
|---|---|---|---|
| ▪ የአየር ፀባይ ተለዋዋጭ ዕለታዊ የአየር ሁኔታ መሆኑን በመግለጽ ፍቺ ይሰጣሉ::<br>▪ ተለዋዋጭ የአየር ሁኔታን ምሳሌ ይሰጣሉ::<br>▪ የአየር ንብረትን የረጅም ጊዜ አማካይ የአየር | 3.1. የአየር ጸባይና የአየር ንብረት (**ክፍለ ጊዜ 9**)<br>3.2. የወረዳችን እጽዋት (**ክፍለ ጊዜ 9**)<br>3.3. የወረዳችን እንስሳት (**ክፍለ ጊዜ 9**)<br>3.4. የወረዳችን የተፈጥሮ ሀብት (**ክፍለ ጊዜ 9**)<br>3.5. የወረዳችን የአካባቢ እንክብካቤ | ▪ ውይይት መጠቀም፣ የተማሪ መጽሐፍ ማንበብ፣ ማሳተፍና በትንሽ ቡድን መሥራት<br>▪ ተማሪዎች ስለአየር ንብረት ምን እንደ ሚያውቁ መጠየቅ<br>▪ ተማሪዎች ምሳሌን በመውሰድ ስለ አየር ሁኔታ (ፀሓያማ፣ ዝናባማ፣ ንፋሳማ፣ ደረቃማ፣ ብርዳማ፣ ሞቃታማ) እንድገልፁ መጠየቅ<br>▪ ተማሪዎች የአየር ንብረትን ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ<br>▪ ተማሪዎች የአየር ንብረት እንደሚቀያየር አስበው እንድወያዩ ማድረግ<br>▪ ተማሪዎች እንደ አካባቢያቸው የአየር ንብረትን ለውጥ ምክንያት የሚሆኑትን እንዲያሳዩ ማድረግ | ▪ ተማሪዎች ለጥያቄዎች የሚሰጡትን መልስ መመልከት<br>▪ የተሻሻሉ ተገባራትን በመከታታል የተለዋዋጭ አየር ሁኔታን የአየር ንብረትን ልዩነት እንድገልፁ መጠየቅ<br>▪ እንደ ምሳሌ የዝናብን በመጠቀም ለመከታተል የሚመች መስጠት<br>▪ ገንቢ ሀሳብን ማቅረብና መመዝገብ<br>▪ የ ዘገባ በመመልከት ገንቢ ሀሳብን ማቅረብና መመዝገብ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፀባይ በማለት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡<br>▪ የአየር ንብረት በዕለት ተዕለት ኑሮዋቸው ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ይናገራሉ፡፡<br>▪ አካባቢያቸው በብዛት የሚገኙትን እፅዋት ይለያሉ፡፡<br>▪ ለእፅዋት እድገት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ይዘረዝራሉ፡፡<br>▪ እፅዋት የሚሰጡትን የተለያዩ ጠቀሜታዎችን ይለያሉ፡፡<br>▪ ለእንስሳት ኑሮ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ይዘረዝራሉ፡፡<br>▪ እንስሳት የጀርባ አጥንት ያላቸው እና የሌላቸው በማለት መለየት | **(ክፍለ ጊዜ 9)** | ▪ በወረዳቸው ዝናብ በብዛት ሚዘንብባቸውን ወራቶች የሚያሳይ ቀላል ግራፍ እንዲያጤኑ ማሳተፍ<br>▪ ለተማሪዎች የቤት ሥራ በመስጠት ሰው በአየር ንብረት ላይ የሚያደርሰውን በጥልቀት እንዲያጠኑ ማድረግ<br>▪ ተማሪዎች በአገራችን ብቻ የሚገኙ እፅዋት እና እንሰሳትን እንድለዩ ማድረግ፡፡ በነዚህ በተቀራራቢ ዘሮች መካከል ያለውን ልዩነት ምሳሌ በመስጠት መግለጽ፡፡<br>▪ እንሰሳትን በአይነታቸውና በአገልግሎቻቸው እንዴት እንደሚንከባከቡና በመኖሪያ ሥፍራቸው መመደብ.<br>▪ በወረዳቸው የሚገኙትን እንስሳትንና እፅዋትን እንድለዩ ማድረግ፡፡<br>▪ ተማሪዎች የአከባቢውን የህብረተሰብ ፍላጎት ለማሟላት አንዳንድ የህብረተሰብ አገልግሎቶችንና እነዚህ አገለግሎቶች ከሌሉ ምን ሊሆን እንደሚችል እንድገልፁ ማድረግ፡፡<br>▪ ተማሪዎች ቅጠልንና የምግብ ትራፊዎችን በመቅበር እፅዋትን ለማሳደግ የሚረዳውን ኮምፖስት እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል እንዲናገሩ ማድረግ፡፡ | ▪ ተከታታይ ምዘና ማካሄድ<br>▪ ተማሪዎችን የእፅዋትእና/ወይም የእንስሳት ባህሪያትን እና እንደ ዋና ሥር ያላቸው፣ ምንቃር ያላቸው፣ ድራድር ሥር ያላቸው ያሉበት አካባቢ እንድኖሩ ያደረጋቸው ምን እንደሆነ ሲወያዩ በመከታታል ችሎታቸውንና ክህሎታቸውን መመዘን፡፡<br>▪ ተማሪዎች በእፅዋት እና እንስሳት መመሳሰልና መለያየት ላይ እንዲናገሩ ማድረግ፡፡<br>▪ እንደሚቃጠል ደን እና በአደጋ ላይ ያለች ወፍ ያሉ እፅዋት እና እንስሳትን ሥዕል መሳልና መለጠፍ<br>▪ የአከባቢውን የህብረተሰብና የተፈጥሮ አካባቢ ግንኙነት ለህብረተሰብ ፍላጎት ከግብ ለማድረስ ትኩረት በመስጠት መግለጽ<br>▪ የአከባቢውን የህብረተሰብ ፍላጎት ለማሟላት አንዳንድ የህብረተሰብ አገልግሎቶችንና እነዚህ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ▪ መልሰዉ ጥቅም ላይ የሚዉሉ እቃዎችን ይለያሉ<br>▪ በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች ይለያሉ፡፡ | | | አገለግሎቶች ከሌሉ ምን ሊሆን እንደሚችል እንድገልፁ ማድረግ፡፡<br>▪ የናሙና ጥያቄዎች:<br>- ቤተሰቦች/ሽ ምግብ ለመግዛት የት ይሄዳሉ? የገበያዉ ቦታ እሩቅ ባይሆን ምን ይፈጠር ነበረ?<br>- የአካባቢዉን ገበያ ማን ይጠቀማል? ለምን አይጠቀሙም? ገበያዉ በአካባቢዉ ባይኖር ኖሮ እነዚህን እቃዎች ለማግኘት ሌላ ምርጫ አለ? ገበያዉ ክዚያ ቢነሳ ምን ያህል ይሰመሀል?<br>- ተማሪዎች የሚጫወቱበት መጫወቻ ባይኖራቸዉ የሚሰማቸዉን እንድገልጹ ማድረግ፡፡ |

| 2ኛ ክፍል: ምዕራፍ 4 | 2ኛ ክፍል: ምዕራፍ 4 ማህበራዊ አካባቢ(ክፍለ ጊዜ 45) | የመማርያ ዘዴዎች | ተከታታይ ምዘና |
|---|---|---|---|
| ▪ የግል ንጽህና አጠባበቅ ጥቅም እንደ እጅ መታጠብ እና ጥርስ መቦረሽን ይግልጻሉ፡፡ | **4.1. የቤተስብ አባላትን እና የሚያስፈልጋጉትን ነገሮች ይገልጻሉ(ክፍለ ጊዜ 19)**<br>▪የቤተስብ የጤና ተጻኢኖ መግለጽ፤ንጽህና፤የሰዉነት | • ይህ የማህበረሰብ ግንኙነትም በሁለት ቡድን በመሆን ፣ በተማሪዎች እና በመምህራን መካከል በሚደረግ ውይይት ስለአካባቢ እና ማህበረሰብ ዕድገት ለመረዳት ወሳኝ ነው፡፡ | በመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ የሚታዩ የግል ንጽህና፤የሰዉንት እንቀስቃሴ ማድረግ እና እረፍት ለምን እንዳስፈለገ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ▪ ለግል እና ለቤተሰብ ንጽህና አጠባበቅ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ይገልጻሉ::<br>▪ በጤና ላይ ተጽኢኖዎችን ይጠቅሳሉ::<br>▪ የት/ቤታቸዉን እና የአካባቢ ማህበረሰባ ቸዉን አባላት ይለያሉ::<br>▪ ተማሪዎች በት/ቤታችዉ ዉስጥ እርስ በርስ ያላችዉ ግንኙነት ያጎለብታሉ::<br>▪ የት/ቤታቸዉን ህገ ደንብ ያከብራሉ:: | እንቅስቃሴ እና እረፍት መዉሰድ/መተኛት/ ላይ ትኩረት መስጠት<br>▪የት/ቤት እና የአካባቢ ማህበረሰብ ምን እንደሚያስፈልጋቸዉ ይለያሉ<br>**4.2 ተማሪዎች ከጓደኞቻቸዉ ጋር ያላቸዉን ግንኙነትና በት/ቤታቸዉ ዉስጥ ያላቸዉን ድርሻ ያሳድጋሉ(ክፍለ ጊዜ 19)**<br>▪ መጫወት እና የሚችሉትን ማከናወን<br>▪ የት/ቤታቸውን ህገደንብ ማክበር<br>**4.3.የግል እና የአካባቢ ንጽህና(ክፍለ ጊዜ 7)**<br>3 የግል እና የአካባቢ ንጽህና እንዴት እንደምንጠብቅ | ▪ ተማሪዎች በሕዝብ አብሮ መኖር ባህል ውስጥ ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ነገሮች የሕዝብን ፍላጎት እንዴት ሊሚላ እንደሚችሉ መግለጽ::<br>▪ ተማሪዎች በቡድን በመሆን በተፈጥሮ ሐብት አጠቃቀም ሁኔታ እና በአካባቢያቸው ከሚገኙ ግንባታዎች የአካባቢው ማህበረሰብ እንዴት መጠቀም እንደሚችል እና ይህ ካልሆነ ደግሞ የማህበረሰቡን ፍላጎት እንዴት ማሟላት እንደሚቻል ይገልፃሉ::<br>▪ የናሙና ጥያቂዎች:ቤተሰብህ/ሽ ምግብ የሚገዘው ከየት ነው? ገበያ እዚያ አካባቢ ባይኖር ኖሮ ምን ይሆን ነበር?<br>▪በአካባቢያቸው በሚገኘውን የመዝናኛ ቦታ የሚጠቀመው ማን ነው? ለምን ይጠቀማሉ? ፓርክ ወይንም የመዝናኛ ቦታ ባይኖር ኖሮ ምን ያደርጉ ነበር?<br>▪ የመጫወቻ ቦታ ቢጎዳ ይሰማሃል/ሻል?<br>▪በማህበረሰብ ስራ ውስጥ የሚሰጡት አገልግሎት እና ከአገልግሎት ጋር ግንኙነት ያላቸው(ለምሳሌ የጽዳት ሰራተኛ፣ የውሃ ንጽህና፣ የIT አገልግሎት) እና ወዘተ እንዴት የማህበረሰብ እና የግል ፍላጎትን ማሟላት እንደሚቻል መግለጽ፣<br>▪ሕዝብ ፍላጎቱን ማሟላትይፈልጋል:: | በጥቅሞቻቸዉ ላይ መወያየት ለምሳሌ ቢያንስ ለ8 ሰዓት ያህል መተኛትን መግለጽ<br>▪ እጃችንን/ሰዉነታችንን በቋሚነት መታጠብ እና የት እንደሚንታጠብ ወይም የት እንደማንታጠብ ላይ በመወያየት ሀሳባችዉን በጽሁፍ ማቅረብ<br>▪ ንጹህ ልብስ የመልበስ ጥቅም ላይ በመወያየት ግጥም መጻፍ<br>▪ አጫጭር ጥያቄዎች<br>▪ ሳምንታዊ እና እለታዊ የጥናት ፕሮግራሞችን ጥቅም መዘርዘር::<br>▪ የተማሪዎች የመናገር ክህሎት: "እኔ ውሃ መዋኘት እወዳልሁ ::ይህ በለሌበት ይከፋኛል ::ሌላ የመዝናኛ ቦታ እሩቅ በመሆኑ መሄድ አልችልም::<br>▪ ተማሪዎችን ስለመሰረታዊ የት/ቤታቸዉ ህግ እና ደንብ መጠይቅ:: |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ▪ተማሪዎች ለጸጉር ፣ ለሰውነት፣ ለጆሮ፣ ለአይን፣ ለአፍንጫ፣ ለጥርስ እና ለእግር ጽዳት በየቀኑ ስራ ላይ በሚውሉት የወረዳቸው የጽዳት እቃዎች ላይ በመመካከር እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>▪የት/ቤታቸዉን ህገና ደንብ ላይ መክበር | |

| 2ኛ ክፍል: ምዕራፍ 5 | 2ኛ ክፍል: ምዕራፍ 5 ልዩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች (ክፍለ ጊዜ 25) | የመመር ዘዴዎች | ተከታታይ ምዘና |
|---|---|---|---|
| • የተለያዩ የትራፊክ ህግ እና ደንብ በመግለጽ ስራ ላይ ያዉላሉ<br>• ተማሪዎች እንደ ኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ካሉ በደም ንክክ ከሚተላለፉ በሽታዎች ራሳቸውን ለመከላከል ጥሩ ባህሪይ ማዳበር አለባቸው:: | **5.1. በመኪና መንገድ ላይ ያለዉ ጥንቃቄ (ክፍለ ጊዜ 12)**<br>**5.2. የመልካም ጥንነት ባህሪይ(ክፍለ ጊዜ 13)**<br>•እንደ ኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ካሉ በደም ንክክ ከሚተላለፉ በሽታዎች ራስን የመከላከል አስፈላጊነት፣ | • ተማሪዎች በአካባቢያቸው የትራፊክ አደጋ ምን ያህል እንደሆነ ትንንሽ ቡድን በመፈጠር ውይይት እንዲያደርጉ ማድረግ፣<br>• ተማሪዎች በደም ንክክ አደገኝነት ላይ ስሜታቸውን እንዲገልጹ ማበረታት:: | • ተማሪዎች የኤች አይ ቪን ብክለት እንዲገልጹ ማድረግ፣<br>• መመልከት እና/ ወይንም የሙከራ ፈተና::<br>• ተማሪዎች በደም ንክክ አደገኝነት ላይ ስሜታቸውን ሲገልጹና ሲወያዩ እውቀታቸውን መመልከት:: |